# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

# የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

# በስትራቴጂክ የመጠባበቂያ እህል ክምችት ኤጀንሲ የምግብ ክምችት አጠባበቅ ስርዓት ውጤታማነትን በተመለከተ የተከናወነ የክትትል ኦዲት ሪፖርት

መጋቢት 2010 ዓ.ም

አዲስ አበባ

## ማውጫ


ማውጫ ..... i

ክፍል አንድ ..... 1

መግቢያ ..... 1

የክትትል ኦዲቱ ዓላማ ..... 2

የክትትል ኦዲቱ ወሰንና ዘዴ ..... 2

የክትትል ኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች ..... 2

ክፍል ሁለት ..... 3

በክትትል ኦዲት ወቅት የተገኙ የኦዲት ግኝቶች፣ ..... 3

በየቅርንጫፍ ፅ/ቤቶች ስር የሚገኙ የምድር ሚዛኖችንበተመለከተ፣ ..... 3

በቅርንጫፍ ፅህፈት ቤቶች ስር የሚገኙ መጋዘኖች እህል ገቢና ወጪ ሲደረግ የሚመዘን መሆኑን በተመለከተ፣ ..... 5

በኤጀንሲው ቅርንጫፍ ፅ/ቤቶች ስር የሚገኙ መጋዘኖች ጥገናን በተመለከተ፣ ..... 7

በኤጀንሲው ስር በሚገኙ መጋዘኖች ላይ በምግብ ነክ ክምችቶች ላይ የሚካሄዱ የጥራት ፍተሻዎችንበተመለከተ፤ ..... 8

የኤጀንሲው ማዕከላዊ ላብራቶሪ እና የምግብ ጥራትና ተባይ ቡድን ባለሙያዎች በቅ/ፅ/ቤቶች ለሚካሄደው የእህል ክምችት ደህንነት ፍተሻን በተመለከተ፤ ..... 10

በኤጀንሲው ቅርንጫፍ ፅ/ቤቶች ስር ባሉ መጋዘኖች የሚገኘው የእህል ክምችት ኦዲት የተደረገውና ያልተደረገው ተለይቶ ሪፖርት የሚደረግ መሆኑንበተመለከተ፣ ..... 11

በኤጀንሲው ስር ያሉ መጋዘኖች አጠባበቅ በተመለከተ ..... 11

በኤጀንሲው ስር የሚገኙ የመጋዘን ኃላፊዎች ስራቸውን የሚያከናውኑባቸው ቢሮዎች በተመለከተ፣ ..... 13

በኤጀንሲው ስር የሚገኙ መጋዘኖች የእሳት አደጋ መከላከያ መሳሪያዎች መኖራቸው በተመለከተ፤ ..... 15

ኤጀንሲው ለተለያዩ ድርጅቶች በብድር የሰጠውን እህል በተመለከተ፤ ..... 17

የኤጀንሲው መረጃ አያያዝ ስርዓትንበተመለከተ፤ ..... 19

አገልግሎት የማይሰጡ ተንቀሳቃሽ የእህል ሚዛኖችን በተመለከተ፤ ..... 20

በአስተዳደሩ ስር በሚገኙ መጋዘኖች ለአደጋ ጊዜ የሚያገለግሉ የስልክ ቁጥሮች በተገቢው ቦታ መቀመጣችን በተመለከተ፣ ........ 21
በኤጀንሲው ስር በሚገኙ መጋዘኖች የእህል ህክምና ከተደረገ በኃላ ስለሚቀሩ ቁሳቁሶች አወጋገድበተመለከተ፣ ........ 22
በኤጀንሲው ስር በሚገኑ መጋዘኖች ለእህል ህክምና የሚጠቀሙበትን መድሃኒት በተመለከተ፣ ........ 24
በኤጀንሲው ቅ/ፅ/ቤቶች ስር በሚገኙ መጋዘኖች አገልግሎት ሊሰጡ የሚችሉ ጄኔሬተሮች መኖራቸውን በተመለከተ፣ ........ 27
ክፍል ሦስት ........ 29
የመደምደሚያ ሀሳብ (Conclusion) ........ 29
3.1 እርምጃ የተወሰደባቸውና መሻሻል የታየባቸው ........ 29
3.2. እርምጃ ያልተወሰደባቸውና መሻሻል ያልታየባቸው ........ 30
ክፍል አራት ........ 33
የማሻሻያ ሀሳቦች (Recommendation) ........ 33

## ክፍል አንድ

### መግቢያ

1. የመጠባበቂያ ምግብ ክምችት በፕሮጀክት መልክ በእርዳታ ማስተባበሪያና ማቋቋሚያ ኮሚሽንስር በ1974 ዓ.ም ተቋቋመ፡፡ በፕሮጀክት መልክ የተቋቋመው ክምችት እንደ አንድ አደጋን ለመከላከል የሚያስችል የዝግጁነት አቅም በአስተማማኝና ቋሚ በሆነ መልክ እንዲቀጥል ለማድረግ በኢትዮጵያየ ሽግግር መንግስት የሚኒስትሮች ምክር ቤት ጥቅምት12ቀን 1987ዓ.ም በወጣ መመሪያ ተጠሪነቱ ለእርዳታ ማስተባበሪያና ማቋቋሚያ ኮሚሽን የሆነ የመጠባበቂያ ምግብ ክምችት አስተዳደር ተብሎ የሚጠራ መንግስታዊ ተቋም እንዲቋቋም ተደርጓል፡፡
2. በቀጣይነትም አስተዳደሩ የተጣለበትን ኃላፊነት በሚገባ እንዲወጣለ ማድረግና በተጨማሪም ምግብ ነክ ያልሆኑ የእርዳታ ቁሳቁሶች ክምችትንም እንዲይዝ ኃላፊነት በመሠጠቱ ጳጉሜ 1 ቀን 1992 ዓ.ም ከሚኒስትሮች ምክር ቤት በወጣ ደንብ ቁጥር 67/1992 ህጋዊ ሰውነት ተሰጥቶት እንደገና እዲቋቋም ተደርጓል፡፡
3. በድጋሚ ተቋሙ ተጠናቅሮ እንዲቀጥል እና ዓላማዎቹን ለማሳካት እንዲችል ተጠሪነቱ ለእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር እንዲሆን በማድረግ በሚኒስቴሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 284/2003 ዓ.ም ስትራቴጂክ ምግብ ክምችት ኤጀንሲ በሚል መጠሪያ ራሱን የቻለ ህጋዊ ሰውነት ያለው መንግስታዊ ተቋም ሆኖ እንዲቋቋም የተደረገ ሲሆን የኤጀንሲው ዋና ዓላማም ስትራቴጂክ መጠባበቂያ ምግብ ክምችትን መያዝና ማስተዳደር እንዲሆን ተደርጓል፡፡
4. ኤጀንሲው በመጠባበቂያነት የሚያዘው ዋና የምግብ ክምችት ዓይነት ስንዴ፣ በቆሎ፣ ማሽላና እንደ አስፈላጊነቱ ሌሎችንም የሚጨምር ነው፡፡ የክምችቱ መጠንም የሚወሰነው በቦርዱ ነው፡፡ የምግብ ክምችቱ የሚገኘው በሰባት የተለያዩ ከተሞች ሲሆን እነሱም አዳማ፣ ሻሸመኔ፣ ሺኒሌ፣ ኮምቦልቻ፣ መቀሌ፣ ወላይታ ሶዶ እና ወረታ ናቸው፡፡
5. ኤጀንሲው የክምችት መጠኑን ለማሳደግ በቀጣይ አመታት ስድስት ተጨማሪ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችን በፍኖተ ሰላም፣ በነቀምት፣ በነገሌ ቦረና፣ በቀብሪዳህር፣ በሆሳዕና እና ባሌ ሮቤ ለመገንባት በዕቅድ የያዘ ሲሆን በፍኖተ ሰላም፣ በቀብሪዳህር እና በሆሳዕና ለሚገነቡ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የቦታ ርክክብና ዲዛይን እና ቅየሳ ስራ በ2009 ዓ.ም በማጠናቀቅ በ2010 በጀት ዓመት ግንባታ ለመጀመር ቅድመ ዝግጅት አጠናቋል፡፡ በሌሎች ማለትም በነቀምት፣ በነገሌ ቦረና እና ባሌ ሮቤ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ለመገንባት ከኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የቦታ ጥያቄ አቅርቦ በመጠባበቅ ላይ ይገኛል፡፡

### የክትትል ኦዲቱ ዓላማ

6. የስትራቴጂክ መጠባበቂያ እህል ክምችት ኤጀንሲ የምግብ ክምችት አስተዳደር በብቃትና በውጤታማነት እየተከናወነ መሆኑን በተመለከተ ከ2000 እስከ 2003 በጀት ዓመት የተከናወነው የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት ላይ የተጠቀሱ ኦዲት ግኝቶች እና የተሰጡ ማሻሻያ ሃሳቦች ላይ የተወሰደ የማስተካከያ እርምጃ መኖሩን እንዲሁም ተገቢውን የክትትል እና የቁጥጥር ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን ለማረጋገጥ ነው፡፡

### የክትትል ኦዲቱ ወሰንና ዘዴ

7. የክትትል ኦዲቱ በዋናኛነት በስትራቴጂክ መጠባበቂያ እህል ክምችት ኤጀንሲ እና በናሙና በተመረጡ 4 በክልል በሚገኙ መጋዘኖች አዳማ፣ ሻሸመኔ፣ ወላይታ ሶዶ እና ወረታ መጋዘን አስተዳደር ቅ/ፅ/ቤቶች እንዲሁም በስሮቻቸው ያሉ 14 መጋዘኖች ላይ የተከናወነ ሲሆን፤ የክትትል ኦዲቱ በ2003 ዓ.ም በተደረገው የክዋኔ ኦዲት መሰረት ከ2004 ዓ.ም እስከ 2010 ዓ.ም ድረስ የምግብ ክምችት አጠባበቅ በተመለከተ በተሰጠው የማሻሻያ ሃሰብ ላይ ትኩረት ያደረገ ነው፡፡

8. የክትትል ኦዲቱ የተከናወነው ከ2005 ዓ.ም በኃላ ያሉትን የስትራቴጂክ እቅድ፤ አመታዊ የእቅድና አፈፃፀም ሪፖርቶች፣ የቅርንጫፍ መጋዘን አስተዳደር ፅ/ቤቶች እና በስራቸው የሚገኙ መጋዘኖች ላይ የተሰሩ የኦዲት እና ኢንስፔክሽን ሪፖርቶች፣ ኤጀንሲውን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ (284/2005)፣ አዋጁን ለማስፈፀም የወጡ የምግብ ክምችት እና አስተዳደር መመሪያ፣ የብድር አሰጣጥና አመላለስ መመሪያ ቁጥር 1/2006፣በክምችት እህሎች ላይ በተለያዩ ምክንያቶች የሚከሰት ጉድለትን በተመለከተ የወጣ መመሪያ ቁጥር 7/1999፣የቦርድ ቃለ ጉባኤ፣ ከተለያዩ ተበዳሪ አካላት ጋር የተደረጉ የብድር ውሎች፣ የመስክ ጉብኝት ሪፖርቶች፣ የቅርንጫፍ አስተዳደር ፅ/ቤቶች ሪፖርቶች እና የመሳሰሉትን ማስረጃዎች በመከለስ ፣ በፅ/ቤቱ እና በመስክ የሚገኙ የሚመለከታቸውን የስራ ኃላፊዎችን ቃለ መጠይቅ በማቅረብ እንዲሁም መጋዘኖች ላይ በአካል ተገኝቶ የመስክ ምልከታ በማድረግ ተከናውኗል፡፡

### የክትትል ኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች

9. የክትትል ኦዲቱን ለማከነወን እንደ መመዘኛ መስፈርት የተመረጡት በቀድሞው ኦዲቱ ወቅት የነበሩ የኦዲት ግኝቶችና የተሰጡ የማሻሻያ ሀሳቦች ናቸው፡፡

## ክፍል ሁለት

### በክትትል ኦዲት ወቅት የተገኙ የኦዲት ግኝቶች፣

### በየቅርንጫፍ ፅ/ቤቶች ስር የሚገኙ የምድር ሚዛኖችንበተመለከተ፣

10. በቀድሞው ኦዲት ወቅት የሻሸመኔ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት መጋዘን የማንዋልና የዲጂታል የምድር ሚዛኖች ቢኖሩትም የማንዋል ሚዛኑ ከ2002 ጀምሮ አገልግሎት መስጠት ማቆሙ፤ የዲጂታል ሚዛኑም አልፎ አልፎ የማተም ችግር ያለበት መሆኑ እና ሚዛኖቹ በትክክል ስለመስራታቸው ክትትል/ ፍተሻ የማይደረግ መሆኑ እንዲሁም የሻሸመኔ እና የአዳማ ቅርንጫፍጽሕፈትቤት መጋዘን ያሉ የምድር ሚዛኖች የኢትዮጵያ እህል ንግድ ድርጅት መሆናቸው በኦዲቱ ታውቀው ነበር ፡፡

11. በዚህም መሰረት ኤጀንሲው በሻሸመኔ እና በአዳማ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች የራሱን የምድር ሚዛን በማሟላት በራሱ የሚዛን ኦኘሬተሮች ወቅታዊ ክትትል ማድረግ እና በመንግሥት ኃላፊነት በተሰጠው አካል የብቃት ማረጋገጫ እንዲያገኙ ማድረግ እንደሚገባው የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ የነበረ ሲሆን በዚሁ መሰረት የተጠቀሱትን ችግሮች ለመቅረፍ ኤጀንሲው የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ሊልክ እና በመርሃ-ግብሩ መሰረት ወደ ሥራ ሊገባ ይገባል፡፡

12. የስትራቴጂክ መጠባበቂያ እህል ክምችት ኤጀንሲ የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት ለፌዴራል ዋና ኦዲተር ኦዲቱ እስከ ተጠናቀቀበት ቀን ድረስ ለሁሉም ግኝቶች ያላከ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡፡፡

13. በክትትል ኦዲቱ ወቅት

- በመቀሌና ኮምቦልቻ መጋዘን አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት የሚገኙ ንብረትነቱ የኤጀንሲው የሆኑ የምድር ሚዛኖች በ2005፣2008 እና 2009 ዓ.ም በሚመለከተው አካል የብቃት ፋተሻ /ካላብሬት/ ስለተደረገላቸው መሻሻል የታየበት መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

ይሁን እንጂ በክትትል በኦዲቱ ወቅት

- የመቀሌ እና የኮምቦልቻ መጋዘን አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት የሚገኙ የምድር ሚዛኖች በ2006፣2007 እና 2010 ዓ.ም በሚመለከተው አካል የብቃት ፍተሻ /ካላብሬት/ ያልተደረገ መሆኑ፣
- የአዳማ መጋዘን አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት በደብዳቤ ቁጥር ቀነ/11/1/219 በቀን 30/07/2007 እና በቁጥር ቀነ/11/00001/257 በቀን 28/11/2008 ለኤጀንሲው

በጸፉት ደብዳቤ በአዳማ ስር የሚገኘው የምድር ሚዛን የኤጀንሲው ንብረት ባለመሆኑ የምድር ሚዛኑ ካላብሬት መደረግ ከነበረበት ጊዜ ያለፈ በመሆኑ ብቃት በማስፈተሽ የብቃት ደረጃውን ማወቅ አለመቻሉን የገለጹ መሆኑ፣

- በወላይታ ሶዶ መጋዘን አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ስር ከሚገኙ 11 ሚዛኖች መካከል ሁለቱ ብቻ ከተስማሚነት ምዘና ድርጅት ብቃት ማረጋገጫ የተሰጣቸው ሲሆን ሌሎቹ ዘጠን (9) ሚዛኖች የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ያልተሰጣቸው መሆኑ ፣
- በናዝሬት/አዳማ መጋዘን አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ስር ከሚገኙ 19 ሚዛኖች ሶስት ብቻ ከኢትዮጵያ ተስማሚነት ምዘና ድርጅት ብቃት ማረጋገጫ የተሰጣቸው መሆኑ
- የወረታ፣ የወላይታ ሶዶ፣የሻሸመኔ መጋዘን አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤቶች በቅርንጫፎቹ የሚገኙት ተንቀሳቃሽ ሚዛኖች የብቃት ማረጋገጫ ፍተሻ ተደርጎላቸው ያማያውቁ መሆኑ፣
- ባለሥልጣኑ ከመቀሌ እና ኮምቦልቻ ቅ/ጽ/ቤቶች በስተቀር በሌሎች ቅ/ጽ/ቤቶች የምድር ሚዛን እንዲኖራቸው አለማድረጉ፣

በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች፣ በቀረበ ቃለ መጠይቅ እና በተደረገ የመስክ ምልከታ ለመረዳት ተችሏል፡፡

14. ስለጉዳዩ የኤጀንሲው ኃላፊዎች በቃለ መጠይቅ፣በረቂቅ ሪፖርት ምላሽ እና በመውጫ ስብሰባ በሰጡት ምላሽ

- የመቀሌና የኮምቦልቻ መጋዘን የምድር ሚዛን ንብረትነቱ የኤጀንሲው በመሆኑ በዓመት ሁለት ግዜ ካሊብሬት የሚያስደረጉ መሆኑን፣
- የአዳማና የሻሸመኔ ቅ/ጽ/ቤት የሚገኙት የምድር ሚዛኖች ንብረትነቱ የኢትዮጵያ የእህል ንግድ ድርጅት በመሆኑ በዓመት አንድ ግዜ ካላብሬት እንደሚደረግና የቅ/ጽ/ቤት ኃላፊዎች ካላብሬት ስለመደረጉም ክትትል እንደሚያደርጉ፣
- የአዳማና የሻሸመኔ ያሉትን የምድር ሚዛኖች ጫና ስለሚበዛበት ቶሎ ቶሎ ስለሚበላሹ በዓመት 2 ግዜ ካላብሬት ለማስደረግ የተስማሙ መሆኑን፣
- የምድር ሚዛኖች በሁሉም ቅ/ጽ/ቤት ቢኖር ሁለት ዓይነት የነበረውን አሰራር የሚያስተካክል በመሆኑ ጠቀሜታው ለተቋሙ እንደሆነ ነገር ግን የምድር ሚዛኑ ከፍተኛ ወጪ የሚጠይቅ በመሆኑ በመደበኛ በጀት ለመግዛት ሙከራ እንዳልተደረገ እና አሁን በስራ ላይ ያሉትም ቢሆንም በእርዳታ የተገኙ መሆናቸውን፣ በአጋር ድርጅቶች በኩል የተለያዩ ፕሮጀክቶች ቀርጸው ማቅረባቸውን እንዲሁም፣

- አዲስ መጋዘን በሚሰራባቸው አካባቢዎች የምድር ሚዛን የዲዛይኑ አካል እንዲሆን ማድረጋቸውንና በመጋዘን ማስፋፊያ እቅዱ መሰረት በሁለተኛው እድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ላይ በሁሉም ቅርንጫፎች የምድር ሚዛኖች ለማስተከል እንደተጠየቀ እና ተንቀሳቃሽ ሚዛኖችም አዲስ በመሆናቸው እና ችግር ስለመኖሩ በቅ/ጽ/ቤቶች ይመርመሩ የሚል ጥያቄ ባለመቅረቡ ያልታዩ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

15. የኤጀንሲው ኃላፊዎች ይህን ይበሉ እንጂ በናሙና ባየናቸው የአዳማውና የሻሸመኔ የምድር ሚዛን ጫና ስለሚበዛበት ቶሎ ቶሎ የሚበላሽ እና ትክክለኛ የክብደት መጠኑን በወረቀት ላይ አትሞ ሲያወጣ የማዛባት ችግር ያለበት በመሆኑ እንዲሁም በናሙና ባየናቸው የወረታ፣ የወላይታ ሶዶ እና የሻሸመኔ መጋዘን አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት የሚገኙ ተንቀሳቃሽ ሚዛኖች መጋቢት 5/2008 ዓ.ም የተገዙ ሲሆኑ ከአንድ ዓመት በላይ ያገለገሉ በመሆናቸው የብቃት ማረጋገጫ ፍተሻ ባለመደረጉ የተሰጠውን ምላሽ አልተቀበልነውም፡፡

16. የምድር ሚዛን በየግዜው ካላብሬት ባለመደረጉ ፣ ሚዛኑም አልፎ አልፎ የማተም እና ሚዛን የማዛባት ችግር የሚያጋጥመው መሆኑ እንዲሁም ተንቀሳቃሽ ሚዛኖች በየጊዜው ካሊብሬት አለመደረጋቸው የቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶቹ ቀልጣፋ አገልግሎት እንዳይሠጡና የመጋዘኖቹ የእህል ገቢና ወጪ ስሌት በትክክል እንዳይታወቅ ሊያደርግና በመጋዘን ሠራተኞቹም ላይ ሚዛኖቹ በሚያሳዩት የስሌት መዋዠቅ ምክንያት የተጠያቂነት ስጋት እንዲፈጠር ያደርጋል፡፡

## በቅርንጫፍ ፅህፈት ቤቶች ስር የሚገኙ መጋዘኖች እህል ገቢና ወጪ ሲደረግ የሚመዘን መሆኑን በተመለከተ፣

17. በሽነሌ፣ በወላይታ ሶዶ እና በወረታ የምድር ሚዛን ባለመኖሩ እህል ሳይመዘን በቆጠራ ብቻ ገቢና ወጪ የሚደረግ መሆኑ በቀድሞው ኦዲት ወቅት ታውቆ ነበር፡፡

18. በዚሁ መሰረት ኤጀንሲው በወላይታ ሶዶ፣በሽነሌ እና በወረታቅርንጫፍጽሕፈትቤቶች እህል በቆጠራ ገቢና ወጪ የሚካሄድው አሠራር ላይ ሊኖር የሚችለውን ክፍተት ለማሻሻል የምድር ሚዛን እንደሚሟላላቸው ማድረግ እንደሚገባ የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

19. በክትትል ኦዲቱ ወቅት፤

- በ2008 ዓ.ም ዕቅድ አፈጻጸም ላይ የምድር ሚዛንን በተመለከተ ከሰባቱ ቅ/ጽ/ቤቶች በሁለት (በመቀሌና በኮምቦልቻ) ቅ/ጽ/ቤቶች ለረዥጀም ጊዜ እያገለገሉ የሚገኙ ሲሆኑ

በወረታ፣ በአዳማ፣ በሻሸመኔ፣ በሸንሌ እና በወላይታ ሶዶ ቅ/ጽ/ቤቶች ኤጀንሲው የራሱ የሆነ የምድር ሚዛን የሌለው በመሆኑ፣

- በሸንሌ፣ በወላይታ ሶዶ እና በወረታ መጋዘን አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት በቅርንጫፎች የምድር ሚዛን ባለመኖሩ እህል በቆጠራ ገቢና ወጪ የሚያደርጉ መሆኑ፣
- የምድር ሚዛን ባለባቸው ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የምድር ሚዛን ቢኖርም እህል ወደ መጋዘን ገቢ እና ወጪ ሲደረግ ባለመመዘኑ በመቀሌ 27,185.3 ኩንታል ፣ በሻሸመኔ 23.4 ኩንታል፣ በኮምቦልቻ 735.13 ኩንታል፣ በአዳማ 3,026.83 ኩንታል በብልጫ የታየ መሆኑ
- የወረታ እና የወላይታ መጋዘን አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት የምድር ሚዛን ባለመኖሩ ወደ መጋዘን የሚገባውና የሚወጣው የማይመዘን እና ጫኝና አውራጅ የጉልበት ሰራተኞች በተለምዶ ሲቀላቸውና ሲጠራጠሩ ብቻ እንዲመዘን መደረጉ፣
- የኤጀንሲው የክምችትና ስርጭትና ዳይሬክቶሬት ኃላፊ ለቀረበላቸው ቃለ መጠየቅ በሰጡት ምላሽ ሚዛን በተመለከተ ግማሽ ቅርንጫፍ መጋዘን በሚዛን ግማሽ ቅርንጫፍ መጋዘን በቁጥር የሚስራበት አሰራር ያለ መሆኑ  መግለጻቸው፡፡

በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና ከቀረቡ መጠይቆች ለማወቅ ተችሏል፡፡

20. ስለጉዳዩ የኤጀንሲው ኃላፊዎች በክትትል ኦዲቱ ወቅት በቃለ መጠየቅ፣ በረቂቅ ሪፖርት እና በመውጫ ስብሰባ ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ፣ አንድ ከረጢት 50 ኪ/ግ መሆኑ የሚያረጋግጡት ወጪና ገቢ ሲሆን ናሙና በመውሰድ በተንቀሳቃሽ ሚዛን እንዲመዘን የሚደረግ መሆኑን፤ ነገር ግን የናሙናዎቹ ክብደት የሚያጠራጥርበት ሁኔታ ሲፈጠር እህሉ ሙሉ በሙሉ እንዲመዘን እንደሚደረግ፣ በቁጥር ገቢ የሆነው እህል መልሶ በቁጥር ወጪ መደረጉን፣ የምድር ሚዛን በሚበላሽበት ወቅት በቁጥር ገብቶ በቁጥር ሲወጣ ብልጫ ሊኖር የሚችል መሆኑን፣ ነገር ግን በሚዛን ገብቶ በሚዛን በሚወጣበት ወቅት ብልጫ ሊታይ እንደማይችል እና የተወሰኑ ቅርንጫፎች መጋዘን በሚዛን በተወሰኑ ቅርንጫፎች በቁጥር የሚሰሩበት አሰራር መኖሩን ገልጸዋል፡፡

21. እህሎች ሳይመዘኑ ወደ መጋዘን የሚገቡና ሳመዘኑ ከመጋዘን የሚወጡ ከሆነ እና ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች እህል በቆጠራ ገቢና ወጪ ማድረጋቸው ለህገወጥ አሠራር ማለትም ኪሎ የማቀናነስ/ ቅሸባ/ እንዲካሄድ ሊያደርግ ይችላል፡፡

**በኤጀንሲው ቅርንጫፍ ፅ/ቤቶች ስር የሚገኙ መጋዘኖች ጥገናን በተመለከተ፣**

22. በቀድሞው ኦዲት ወቅት በወላይታ ሶዶና በመቀሌ ቅርንጫፍ ፅ/ቤቶች የጥገና ባለሙያ ባለመኖሩ የሚያፈሱ መጋዘኖች አለመጠገናቸው ና በክምችት እህሉም ላይ ጉዳት የደረሰ መሆኑ ታውቆ ነበር፡፡

23. የስትራቴጂክ መጠባበቂያ እህል ክምችት ኤጀንሲ በወላይታ ሶዶና በመቀሌ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች የመጋዘን ጥገና ባለሙያዎችን በማሟላት ወይም በውጪ ባለሞያ በመጠቀም ጥገና የሚያስፈልጋቸው መጋዘኖች በዝናብ ምክንያት በክምችቱ ላይ ጉዳት ከማድረሳቸው በፊት ጥገና ሊደረግላቸው እንደሚገባ የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

24. በክትትል ኦዲቱ ወቅት

- በወረታ መጋዘን አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ስር ያሉ የእህል መጋዘኖች የጣሪያ ፍሳሽ ያለባቸው በመሆኑ ስፋቱና ቁመቱ 16 በ13 ሜትር በሆነ ሰማያዊ ሸራ የጣሪያ ፋሳሹን ለመከላከል እስቶክ (ክምችት) አናት ላይ በዝናብ ወቅት ለማልበስ ለኤጀንሲው የግዥ ጥያቄ ያቀረቡ መሆኑ፣እንዲሁም ከ2005 እስከ 2009 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ በሻሸመኔ፣ በወረታ እና በአዳማ ቅርንጫፉ ጽ/ቤቶች በሚገኙ የእህል መጋዘን በመጋዘኑ ውስጥ የጣራ ፍሳሽ በመኖሩ እህሉ እንዳይበላሽ ሸራ ሸፍነው እየሰሩ መሆኑ፣
- የአዳማ መጋዘን አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት የስራ ኃላፊ እና የክምችት ቡድን መሪ መጋዘንን አስመልክቶ ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት ምላሽ በ2008 ዓ.ም መጋዘን ቁጥር 36 እና 37 በውጪ ባለሙያ ጥገና የተደረገላቸው ቢሆንም ስራው ውጤታማ ባለመሆኑ ተመልሰው የሚያፈሱ ፣
- የወላይታ ሶዶ መጋዘን አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት የሚገኙ የሸራ መጋዘኖች (Rubhaill) ለ8 ዓመት ታስቦ የተሰራ ቢሆንም 20 ዓመት ያስቆጠረ በመሆኑ በዝናብ ወቅት የዝናብ ፋሳሽ ለመከላከል በእስታኩ (ክምችት) አናት ላይ ላስቲክ በማልበስ የሚጠቀሙ መሆኑ፣

ከተከለሱ ማስረጃዎች፣ ከቀረቡ ቃለ መጠይቆች እና በመስክ ምልከታ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

25. ስለጉዳዩ የኤጀንሲው ኃላፊዎች በክትትል ኦዲቱ ወቅት በቃለ መጠየቅ፣ በረቂቅ ሪፖርት እና በመውጫ ስብሰባ በሰጡት ምላሽ፣

- በወረታ ቅርንጫፋ ጽህፈት ቤት እና በአዳማ ቅርንጫፋ ጽህፈት ቤት መጋዘን ቁጥር 36 እና መጋዘን ቁጥር 37 የተለየ ችግር ያለበት በመሆኑ ከዚህ በፊት በጀት ተይዞለት ተጠግኖ እንደነበር ነገር ግን ጣራው አሮጌ በመሆኑ የሚያፈሰውን ቦታ ለመጠገን ሲሞከር ሌላ ቀዳዳ እየፈጠረ መቸገራቸውን፣
- በፊት በየቅርንጫፉ ጽ/ቤቱ የጥገና በጀት የሚያዝ ቢሆንም ችግሩን መቅረፋ ባለመቻሉ በጀት በማዕከል ደረጃ በዚህ ዓመት ተይዞ የወረታና የአዳማን መጋዘን ለማስጠገን ታቅዶ የነበረ ሲሆን በጀቱ ስላልበቃቸው በዚህ ዓመት በወረታ ሁለት መጋዘኖች ላይ ከዚህ በፊት ለመጋዘኖቹ ጥቅም ላይ የዋለው የቆርቆሮ አይነት ውጤታማ ባለመሆኑ በአዲስ በK SPAN የቆርቆሮ አይነት በመቀየር ሙከራ እንደሚደረግና ውጤታማ ከሆነ ሙሉ በሙሉ የሌሎች መጋዘኖች የቆርቆሮ ክዳን በመቀየር በK SPAN የቆርቆሮ አይነት ለማስጠገን እየሰሩ እንደሚገኙ፣
- በአዳማ መጋዘን ቁጥር 36 እና 37 ሙሉ በሙሉ ከስራ ውጪ እንዳልሆኑና አሁንም ፍሳሽ ባለበት ቦታ ሸራ እያለበሱ የሚጠቀሙ መሆኑን እና በቅ/ጽ/ቤቶች የሚገኙ የሸራ መጋዘኖችን በፊት በጊዜያዊነት የተሰራ ስለሆነ አሁን ሙሉ በሙሉ በማርጀቱ ለማንሳትና በአዲሱ ማስፋፊያ በብሎኬት ለመስራት እንዳቀዱ

ገልፀዋል፡፡

26. የመጋዘንጥገና ባለሙያዎች በቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች ያሉ ቢሆንም ጥገናው ከቅርንጫፎች አቅም በላይ በመሆኑ በዝናብ ወቅት አብዛኛውን መጋዘን የሚያፈሱ በመሆናቸው በክምችት የተያዘውን እህል በዝናብ ምክንያት እንዲበላሽ ያደርጋል፡፡

## በኤጀንሲው ስር በሚገኙ መጋዘኖች ላይ በምግብ ነክ ክምችቶች ላይ የሚካሄዱ የጥራት ፍተሻዎችንበተመለከተ፤

27. በናሙና በታዩ ቅ/ፅ/ቤቶች የእህል ጥራትና ተባይ ቁጥጥር ቴክኒሻኖች በመመሪያው መሰረት ወጥነት ባለው መልኩ በወር 1 ጊዜ ፍተሸ የማያካሂዱ እና ተባይ ሊከሰት ይችላል ብለው በሚያስቡበት ጊዜ ብቻ የሚፈትሹ መሆኑ በቀድሞው ኦዲት ታውቆ ነበር፡፡

28. በዚህም ኤጀንሲው በሁሉም ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች የሚገኙ የእህል ጥራትና ተባይ ቁጥጥር ቴክኒሻኖች ባዘጋጀው መመሪያ መሠረት ወጥነት ባለውና በተመሣሣይ ሁኔታ የጥራት ፍተሻ በወር አንድ ጊዜ እንዲያከናውኑ ማድረግ እንደሚጠበቅበት የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

29. በክትትል ኦዲቱ ወቅት

- በአዳማ መጋዘን አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት በመመሪያው መሰረት ወጥነት ባለው መልኩ ቁጥጥር ባለመደረጉ በመጋዘን ቁጥር 13 እና 15 ተባይ የታየ መሆኑና በመጋዘን ቁጥር 13 የመጀመሪያው ህክምና በ14/01/2009 ዓ.ም የተሰጠ ቢሆንም በአጭር ጊዜ ውስጥ በድጋሚ ተባይ በእህል መጋዘኑ ውስጥ መከሰቱ በህዳር 2009 ዓ.ም በተከናወነ የመስክ ሪፓርት ግብረ መልስ ላይ መገለጹ፣
  - በወላይታ ሶዶ መጋዘን አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት መጋዘን ቁጥር 7 የመጀመሪያ ህክምና ከተደረገለት 6 ወር ያለፈው ሲሆን በመጋዘኑ ውስጥ ራይዞ ፔርታ እና ኪራፕቶለስስ ተባይ በእስቶኩ ላይ የታየ በመሆኑ በአስቸኳይ ወደ ህክምና እንዲገባ የተደረገ መሆኑ በህዳር 2009 ዓ.ም በተከናወነ የመስክ ሪፓርት ግብረ መልስ ላይ መገለጹ፣
  - በመቀሌ መጋዘን ቁጥር 1 እህሉ ገቢ ከሆነ ከ3 -6 ወር ጊዜ ያስቆጠረ ቢሆንም በአጭር ጊዜ ውስጥ ሁለት ጊዜ እንዲታከም መደረጉ፣
  - በሽንሌ መጋዘን ቁጥር 1 ከአለም ምግብ ፕሮግራም ገቢ የሆነው እህል በቀን 22/1/2009 ዓ.ም ተባይ ተገኝቶ የታከመ ቢሆንም እህሉ ከታከመ በኃላ በ49ኛ ቀን ውስጥ በድጋሚ ራይዞ ፔትራ ተባዮች መገኘታቸው፣ በመጋዘን ቁጥር 4 የሚገኘው እህል ከታከመ 71 ቀን ቢሆነውም በድጋሚ ተባይ የተከሰተ መሆኑ በህዳር 2009 ዓ.ም በተከናወነ የመስክ ግብረ መልስ ሪፓርት ላይ መገለጹ፣
  - የእህል ጥራትና ተባይ ቁጥጥር ቴክኒሻኖች በመመሪያው መሰረት ወጥነት ባለው መልኩ በወር 1 ጊዜ በቅርንጫፋ ጽ/ቤት ፍተሻበማካሄድ ሪፖርት መቅረብ ያለበት ቢሆንም ከ2005 — 2010 ዓ.ም ባለው ጊዜያት ውስጥ በመቀሌ ቅ/ጽ/ቤት የ2 ወር፣ በሽንሌ ቅ/ጽ/ቤት የ13 ወር ፣ ወላይታ ሶዶ ቅ/ጽ/ቤት የ11 ወር፣በኮምቦልቻ ቅ/ጽ/ቤት የ15 ወር ፣ በአዳማ ቅ/ጽ/ቤት የ4 ወር ፣በሻሸመኔ ቅ/ጽ/ቤት የ7 ወር እና በወረታ ቅ/ጽ/ቤት የ6 ወርየጥራት ፍተሻ ሪፖርት ብቻ በኦዲቱ ወቅት ተጠይቆ መቅረብ መቻሉ፣

ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

30. ስለጉዳዩ የኤጀንሲው ኃላፊዎች በክትትል ኦዲቱ ወቅት በቃለ መጠየቅ፣ በረቂቅ ሪፖርት እና በመውጫ ስብሰባ በሰጡት ምላሽ፣ በቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት የእህል ጥራትና ተባይ ቁጥጥር ቴክኒሻኖች በየወሩ ፍተሻ አድርገው ሪፖርት ለኤጀንሲው እንደሚልኩና የሪፖርቶቹ ናሙና በኤጀንሲው እንደሚገኝና ማየት እንደሚቻል ገልፀዋል፡፡

31. የኤጀንሲው ኃላፊዎች ይህን ይበሉ እንጂ የእህል የቅርንጫፍ ጥራትና ተባይ ቁጥጥር ቴክኒሻኖች በመመሪያው መሰረት ወጥነት ባለው መልኩ በወር 1 ጊዜ ስለማድረጋቸው

ውስን የኢንፔክሽን ሪፖርት የቀረበ በመሆኑና እህሉ ህክምና ከተደረገ በኃላ በአጭር ጊዜ ተባይ እየታየ በመሆኑ በመስክ ግብረ መልስ ሪፖርት ላይ የተገለጸ በመሆኑ የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያስቸግራል።

32. በሁሉም ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች የሚገኙ የእህል ጥራትና ተባይ ቁጥጥር ቴክኒሻኖች በአስተዳደሩ መመሪያ መሰረት ወጥነት ባለው መልኩ የጥራት ፍተሻውን በወር አንድ ጊዜ የማያከናውኑ ከሆነ ከጥራት ፍተሻው የሚጠበቀውን ውጤት እንዳያስገኝ እንዲሁም ሁሉም ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች በሚጠበቀው ደረጃ እየሠሩ መሆኑን ለመከታተል እና ለማረጋገጥ የማያስችል ከመሆኑም በላይ በተገኙ ድክመቶች ላይ የእርምት እርምጃ እንዳይወሰድባቸውና አሠራራቸውም እንዳይሻሻል ያደርጋል።

## የኤጀንሲው ማዕከላዊ ላብራቶሪ እና የምግብ ጥራትና ተባይ ቡድን ባለሙያዎች በቅ/ፅ/ቤቶች ለሚካሄደው የእህል ክምችት ደህንነት ፍተሻን በተመለከተ፤

33. በሽንሌ፣ በወላይታ ሶዶ፣ በአዳማ፣ በመቀሌና ሻሸመኔ የሚገኙ የእህል ተባይና ጥራት ቁጥጥር ኃላፊዎች ከማዕከላዊ ላብራቶሪ አገልግሎት ጋር በመሆን በቅንጅት በየሩብ አመቱ በመገኘት የእህል ክምችት ደህንነት የጥራት ፍተሻ ስራ አለማካሄዳቸው በቀድሞው ኦዲት ወቅት የታየ ክፍተት ነው።

34. የስትራቴጂክ የመጠባበቂያ እህል ክምችት ኤጀንሲ ማዕከላዊ ላብራቶሪና የምግብ ጥራትና ተባይ ቁጥጥር የባለሙያዎች ቡድን በቅንጅት በየሩብ ዓመቱ በሁሉም ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች በመገኘት የጥራት ፍተሻ ሥራ በአግባቡ ማከናወን እንደሚገባቸው የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ ነበር።

35. በክትትል ኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው በታዩ የመጋዘን አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የእህል ክምችትና ስርጭት ዳይሬክቶሬት እና የጥራት ቁጥጥር ስራ አመራር ዳይሮክቶሬት በቅንጅት በቅ/ጽ/ቤት በመገኘት የእህል ክምችት ደህንነት የጥራት ፍተሻ ስራ የሚያካሂዱ በመሆኑ እንዲሁም የእህል ክምችት አያያዝን በማየት ጠንካራና ደካማ ጎን በመለየት በአካል ተግኝቶና በጽሁፍም ግብረ መልስ የሚሰጥ በመሆኑ የተሻሻለ እንደሆነ ለማወቅ ተችሏል።

## በኤጀንሲው ቅርንጫፍ ፅ/ቤቶች ስር ባሉ መጋዘኖች የሚገኘው የእህል ክምችት ኦዲት የተደረገውና ያልተደረገው ተለይቶ ሪፖርት የሚደረግ መሆኑንበተመለከተ፣

36. በአዳማ፣ በኮምቦልቻ፣ በሻሸመኔ፣ በወላይታ ሶዶና በሽንሌ የሚገኙ ቅ/ፅ/ቤቶች መጋዘኖች የሚገኘው የእህል ክምችት ኦዲት የተደረገውና ያልተደረገው መጠን ተለይቶ በሪፖርት ማቅረቢያ ቅፅ ላይ ተሞልቶ በየ3 ወሩ ሪፖርት አለመደረጉ በቀድሞው ኦዲት ወቅት ተገኝቶ ነበር፡፡

37. በኤጀንሲው ቅ/ጽ/ቤቶች ስር በሚገኙ መጋዘኖች የሚገኘው የእህል ክምችት ኦዲት የተደረገውና ያልተደረገው መጠን ተለይቶ በሪፖርት ማቅረቢያ ቅፅ ላይ ተሞልቶ በየሦስት ወሩ ሪፖርት መደረግ ንደሚኖርበት የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ ነበረ፡፡

38. በክትትል ኦዲቱ ወቅት፤

- ኤጀንሲው የእህል ክምችት ኦዲትን አስመልክቶ አዲስ አሰራር የዘረጋ በመሆኑ በመጋዘን ውስጥ እህል ገብቶ ሙሉ በሙሉ ወጪ ሆኖ ሳይጠናቀቅ የሚደረገው ኦዲት በመጋዘኑ ውስጥ የሚቀመጠው የእህል ክምችት በርካታ በመሆኑ ኦዲት ለማድረግ አስቸጋሪ ከመሆኑም በላይ ኤጀንሲውን ለተጨማሪ ወጪ (ጉልበት ሰራተኛ ክፍያ) የሚዳርግ በመሆኑ በመጋዘን የገባው እህል ሙሉ በሙሉ ወጪ ሆኖ ሲያልቅ ኦዲት መደረጉ የተሻሻለ እንደሆነ ለማወቅ ተችሏል፡፡

## በኤጀንሲው ስር ያሉ መጋዘኖች አጠባበቅ በተመለከተ

39. በቀድሞው ኦዲት ወቅት በሻሸመኔ፣ በአዳማ፣ በወላይታ ሶዶ፣ በሽንሌና በኮምቦልቻ የሚገኙ የእህል መጋዘኖች ውስጥ ሌሎች ቁሳቁሶች፡- የተበላሹ ተንቀሳቃሽ ሚዛኖች፣ ወንበሮች፣ የፅዳት ዕቃዎችና ቆርቆሮዎች መቀመጣቸው ተገኝቶ ነበር፡፡

40. በዚሁ መሰረት ኤጀንሲው በቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች ስር በሚገኙ የእህል ማከማቻ መጋዘኖች ውስጥ ሌሎች ቁሳቁሶች እንዳይቀመጡና መጋዘኖቹም በንጽሕና እንዲጠበቁ ማድረግ እንደሚጠበቅበት የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

41. በክትትል ኦዲቱ ወቅት፤

- በ2009 ዓ.ም በሻሸመኔና በወላይታ ሶዶ መጋዘን የኤጀንሲው ንብረት ያልሆኑና በሰነድ ያልተመዘገቡ የሌላ መ/ቤት ንብረት የሆኑ ዱቄት፣ጥራጥሬ እና ዘይት ከኤጀንሲው እህል ጋር በአንድ መጋዘን ተቀላቅለው የተቀመጡ መሆኑ በኤጀንሲው የክዋኔ ኦዲት ሪፓርት ላይ መረጋገጡ፣

- በክትትል ኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩ በወላይታ ሶዶ፣ በአዳማ፣በሻሸመኔ መጋዘን አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤቶች ስር በሚገኙ የእህል መጋዘኖች ውስጥ የተለያዩ ወንበሮች፣ ጠረጴዛዎች፣ ፋይል ካብኔት፣ ልብሶች፣ ጫማዎች፣ ዕቃ የያዙ ካርቶኖች፣ ባለ 5 እና ባለ 20 ሊትር ጄሪካኖች፣ የቤት ቁሳቁሶች ማለትም የልብስ ሳጥኖች፣ የምግብ መሶብ፣ በልብስ የተሞሉ ማዳበሪያዎች እና እና የጽዳት ዕቃዎች የተቀመጡ መሆኑ፣

ከተከለሱ ማስረጃዎች እና በመስክ ምልከታ ለማወቅ ተችሏል ።



ፎቶ ቁጥር1 ፡- በአዳማ፣ሻሸመኔ እና ወላይታ ሶዶ ቅ/ጽ/ቤት በእህል ክምችት መጋዘኑ ውስጥ የተለያዩ ወንበሮች፣ጠረጴዛዎች፣ፋይል ካብኔት፣ልብሶች፣ ጫማዎች፣ ዕቃ የያዙ ካርቶኖች፣ባለ 5 እና ባለ 20 ሊትር ጄሪካኖች ፣የቤት ቁሳቁሶች

42. ስለጉዳዩ የኤጀንሲው ኃላፊዎች በክትትል ኦዲቱ ወቅት በቃለ መጠየቅ፣ በረቂቅ ሪፖርት እና በመውጫ ስብሰባ ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ፣ የምግብ ዘይትና ዱቄትን በተመለከተ በሀገሪቱ ከ2 ዓመት ወደዚህ በሰው ሰራሽና በተፈጥሮ በርካታ ተረጂዎች በመኖራቸው ለእርዳታ የሚውል እህል ሲጫን ዘይትና ዱቄት አብሮ ተቀላቅሎ መጫን ስላለበት ንብረትነቱ የሌላ መንግስታዊ ተቋም ቢሆንም በባዶ ሸራ መጋዘን እንዲቀመጥ የተስማሙ እንደሆነ፣ በሌሎች መጋዘኖች የሚገኙ ቁሳቁሶችን በተመለከተ በጊዜያዊነት ከማዕከላዊ መጋዘን ተጭነው ሲመጡ እስከሚከፋፈል ድረስ ተቀምጦ ሊሆን እንደሚችል እንጂ በመጋዘኑ ውስጥ ባዶም ቢሆን ምንም ዓይነት ቁሳቁስ መቀመጥ የሌለበት መሆኑን ገልፀዋል፡፡

43. በእህል ማከማቻ መጋዘኖች ውስጥ የተለያዩ ቁሳቁሶች መቀመጣቸው የእህል ገቢና ወጪ በሚኖርበት ወቅት በተፈለገ ሁኔታ ለመንቀሳቀስ የሚያስቸግር ከመሆኑም በላይ ለተባይ መራቢያነት ምቹ ሁኔታን ሊፈጥር ስለሚችል በየመጋዘኖቹ ውስጥ የተከማቸው እህል በተባይ እንዲጠቃያደርጋል፡፡

## በኤጀንሲው ስር የሚገኙ የመጋዘን ኃላፊዎች ስራቸውን የሚያከናውኑባቸው ቢሮዎች በተመለከተ፣

44. በቀድሞው ኦዲት ወቅት በሻሸመኔ፣ በአዳማ፣በወላይታ ሶዶ፣ በሽንሌ፣ በመቀሌ ና በኮምቦልቻ በሚገኙ መጋዘኖች የሚሰሩ የመጋዘን ኃላፊዎች እና ሰራተኞች የመጋዘኑን ገቢና ወጪ እንቅስቃሴና ሌሎች ስራዎች የሚያካሂዱበት የተለየ ቢሮ አለመኖሩና በእህል መጋዘኖች ውስጥ የሚቀመጡበት ሁኔታ መኖሩ ታይቷል፡፡

45. በቀድሞው ኦዲት ኤጀንሲው በቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች ስር በሚገኙ መጋዘኖች የሚሠሩ የመጋዘን ኃላፊዎች ቢሮ ከመጋዘኑ ውጭ የተለየ ክፍል እንዲሆን ማድረግ እንደሚገባው የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቷል፡፡

46. በክትትል ኦዲቱ ወቅት፤

- በወላይታ ሶዶ ቅርንጫፉ ጽ/ቤት በሚገኙ መጋዘኖች ለሚሰሩ የመጋዘን ክለርኮችና እና ጽዳት ሰራተኞች የእለት ተዕለት ስራዎች የሚያካሂዱበት ከመጋዘኑ ውጪ የተለየ ቢሮ መሰራቱ የተሻሻለ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

ይሁን እንጂ በክትትል ኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩ፡-

- የአዳማ፣ በወረታ እና በሻሸመኔ መጋዘን አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ለመጋዘን ኃላፊዎች፣ ጸሀፊና የጽዳት ሰራተኞች የዘውትር ስራቸውን የሚያከናውኑበት ከመጋዘኑ ውጪ የተለየ ቢሮ የሌላቸው መሆኑ፣

- በአዳማ፣ በወረታ፣ በሻሸመኔ፣ በወላይታ ሶዶ መጋዘን አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት በመጋዘኑ ውስጥ አባራ እየቦነነ እና ለእህል ህክምና የሚጠቀሙበት መድኃኒት ሽታውና የኬሚካሉ ጋዝ ባለበት ቦታ እንደ ቢሮ በመገልገል ተቀምጠው እየሰሩ የሚገኙ መሆኑ፣
- የወላይታ ሶዶ መጋዘን አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ለመጋዘን ክለርኮችና የጽዳት ሰራተኞች ከመጋዘኑ ውጪ የተለየ ቢሮ የተሰራላቸው ቢሆንም ለመጋዘን ኃላፊዎች ግን ከመጋዘኑ ውጪ የተለየ ቢሮ የሌላቸው መሆኑ፣

በኦዲቱ ወቅት ከተደረገ ቃለ መጠይቅ እና የመስክ ምልከታ ለመረዳት ተችሏል።



ፎቶ ቁጥር 2 :- በወረታ፣በአዳማ፣በሻመኔ እና ወላይታ ሶዶ የመጋዘን ኃላፊዎች፣ሰራተኞች እና ሳንቴሽን ባለሙያዎች ከቁሳቁስ ጋር በጋራ የሚሰሩበት ቢሮ

47. ስለጉዳዩ የኤጀንሲው ኃላፊዎች በክትትል ኦዲቱ ወቅት በቃለ መጠየቅ፣በረቂቅ ሪፖርት እና በመውጫ ስብሰባ ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ፣ የቢሮ ግንባታ በተደጋጋሚ ከቅ/ጽ/ቤቶች የሚጠየቅ እንደሆነና ለመጋዘን ሰራተኞች፣ለክለርኮችና ጽዳት ሰራተኞች የተለየ ቢሮ ለመስራት ካፒታል በጀት ጠይቀው በጀት እንዳልተፈቀደላቸውና እንደ አማራጭ የወሰዱት እርምጃ በተገኘው ማቴሪያል በቆርቆሮ ለጽዳት ሰራተኞች ቢሮ እየተሰራ እንደሆነ፣በአዲሱ ማስፋፊያ ዲዛይን ላይ ለመጋዘን ሰራተኞች፣ ለክለርኮችና ጽዳት ሰራተኞች የተለየ ቢሮ እንዲኖራቸው አካተው የጠየቁ መሆኑን ገልፀዋል።
48. በቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች ስር ባሉ መጋዘኖች ለሚሠሩ የመጋዘን ሃላፊዎች ስራቸውን የሚያካሂዱበት ቢሮ በመጋዘኖቹ ውስጥ መሆኑ የእህል መናድ ቢያጋጥም እንዲሁም ከእህል ህክምና ከሚውል መድሃኒት ርጭት ጋር በተያያዘ በሚፈጠር ሽታ እና

በመጋዘኑ ውስጥ በሚኖር አቧራ በሠራተኞቹ ጤንነት ላይ ጉዳት ሊያስከትል ይችላል፡፡ እንዲሁም የመጋዘን ኃላፊዎች የስራ ዶክንሜንቶችን ለማስቀመጥ ችግር የሚፈጥር ይሆናል፡፡

## በኤጀንሲው ስር የሚገኙ መጋዘኖች የእሳት አደጋ መከላከያ መሳሪያዎች መኖራቸው በተመለከተ፤

49. በቀድሞው ኦዲት ወቅት በየመጋዘኖቹ ቢያንስ 2 የእሳት አደጋ መከላከያ መሳሪያ መኖርና ስለመስራታቸው መረጋገጥ ቢኖርበትም በናሙና በታዩ መጋዘኖች የሳት አደጋ መሳሪያ ያልተሟላ መሆኑ፤ ስለመስራታቸው አለመረጋገጡ እና አጠቃቀማቸውን የሚያውቅ ሰራተኛ አለመኖሩ የተገኙ ግኝቶች ነበሩ፡፡

50. የስትራቴጂክ መጠባበቂያ እህል ክምችት ኤጀንሲ በቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶቹ ስር በሚገኙ መጋዘኖች በቂ የሳት አደጋ ማጥፊያ መሣሪያዎች በማሟላት ለመሣሪያዎቹም ወቅታዊ ጥገናና ፍተሻ ማድረግ እንደሚገባው የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

በክትትል ኦዲቱ ወቅት፤

- የአዳማ መጋዘን አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት በቁጥር ቀነ/11/1246 በቀን 05 ታህሳስ 2010 ዓ.ም ለኤጀንሲው በጻፈው ደብዳቤ በንብረት ክፍል ተለያዩ የእሳት አደጋ መከላከያ ሲሊንደሮች እንደሚገኙና መታደስ እንዳለባቸው የሚታወቅ ቢሆንም በተደጋጋሚ በቁጥር ቀነ/11/1/231 በቀን 17/4/2009 እና በቁጥር ቀነ/11/1/235 በቀን 3/12/2009 ዓ.ም እንዲሁም በ2010 ዓ.ም 2 ጊዜ ደብዳቤ ቢጻፍም ትኩረት ተሰጥቶት እንዲታደስ (ሰርቪስ እንዲደረግ) አለመደረጉ፣
- በአዳማ፣የወላይታ ሶዶ እና የሻሸመኔ መጋዘን አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤቶች ከ2008 ዓ.ም ወዲህ ለመጋዘን ሰራተኞቹ በእሳት አደጋ መሳሪያ አጠቃቀም ዙሪያ ስልጠና ተሰጥቶ የማያውቅ መሆኑ እና በፊት ስልጠና የወሰዱ ባለሙያዎች በቦታው ባለመኖራቸውአሁን በስራው ላይ ያሉ ግንዛቤ የሌላቸው መሆኑ፣
- በወረታ መጋዘን በቅ/ጽ/ቤቱ ውስጥ በሶስቱ ሼራ መጋዘን (ራቦሎች)፣በወላይታ ሶዶ በሶስቱ ሼራ መጋዘን (ራቦሎች)፣ በኮምቦልቻ መጋዘን በመጋዘን ቁጥር 1 እና 2 ምንም የእሳት አደጋ መከላከያ መሳሪያ የሌለ መሆኑ፣
- በአዳማና መጋዘን አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ስር በሚገኘው የኤጀንሲው የማዕከሉ የዕቃ መጋዘን ውስጥ የተለያዩ መጠንና አይነት ያላቸው አዲስና አገልግሎት የሰጡ የእሳት ማጥፊያ ሲሊንደሮች የሚገኙ ሲሆን በየ6 ወሩ ሰርቪስ መደረግ

ቢኖርባቸውም እ.ኤ.አ በ26/5/2011 እና በ09/06/2013 ሰርቪስ እንደተደረገላቸው ተከማችተው መገኘታቸው፣

- በወላይታ ሶዶ ቅ/ጽ/ቤት በሽራ መጋዘኑ ውስጥ የነበሩ የእሳት አደጋ መከላከያ መሳሪያ ሲሊንደሮች ተሰብስበው በዕቃ መጋዘን ውስጥ እንዲቀመጥ መደረጉ፣

ከተከለሱ ማስረጃዎች፣ ከቀረበ ቃለ መጠይቅ እና በተደረገ መስክ ምልከታ ለማወቅ ተችሏል፡፡



ፎቶ ቁጥር 3 ፡- በወረታ፣በአዳማ፣በሻሸመኔ ቅ/ጽ/ቤት እድሳት/ሰርቪስ ያልተደረገለት፣ ምንም አይነት ጽሁፍ የሌለው እንዲሁም በክምችት ያለ አገልግሎት የተቀመጡ የእሳት አደጋ ማጥፊያ መሳሪያ

51. ስለጉዳዩ የኤጀንሲው ኃላፊዎች በክትትል ኦዲቱ ወቅት በቃለ መጠየቅ፣ በረቂቅ ሪፖርት እና በመውጫ ስብሰባ ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ፣ የቅ/ጽ/ቤቶች ዋና ስራ የሀገሪቱን ንብረት መያዝና መጠበቅ ሲሆን ኤጀንሲው ከቅ/ጽ/ቤት የሚቀርብለትን ጥያቄ እያየ ማሟላት እንደሆነና የእሳት አደጋ መሳሪያዎቹ አንዱ የእህል ደህንነቱን የሚጠበቅበት በመሆኑ በየግምጃ ቤቱ መሳሪያዎች ተሰብስበው የተቀመጡ ከሆነ ይህንን እንደ ድክመት የሚያዩት መሆኑን እና የእሳት አደጋ መሳሪያዎች ስለመኖራቸው እንጂ ስለመስራቱ ክትትል አለማድረጋቸውን በቀጣይ አስፈላጊውን ማስተካከያ እንደሚያደርጉ ገልፀዋል፡፡

52. ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶች ሥር በሚገኙ መጋዘኖች በቂ የእሳት አደጋ ማጥፊያ መሣሪያዎች ወቅታዊ ጥገናና ፍተሻ እየተደረገላቸው ተሟልተው ካልተገኙ ለሚመለከታቸው ሰራተኞች በመሳሪያው አጠቃቀም ዙሪያ ስልጠና ካልተሰጠ በመጋዘኖቹ በአጋጣሚ የእሳት አደጋ ቢከሰት በኤጀንሲው ክምችት ላይ ከፍተኛ ጉዳት ሊያስከትል ይችላል፡፡

## ኤጀንሲው ለተለያዩ ድርጅቶች በብድር የሰጠውን እህል በተመለከተ፤

53. በቀድሞው ኦዲት ወቅት በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የዋስትና ደብዳቤ ለግብርና ሚኒስቴር የሴፍቲ ኔት ኘሮግራም ማስፈፀሚያ እና በአውሮፓ ህብረት ዋስትና ለአደጋ መከላከልና ዝግጁነት የምግብ ዋስትና ዘርፍ ከክምችቱ በብድር የተሰጠ እህል በወቅቱ የማይመለስ መሆኑ ተገኝቶ ነበር፡፡

54. ኤጀንሲው ከክምችቱ ለተለያዩ ድርጅቶች በብድር የሚሰጠው እህል በወቅቱ እንዲመለስ የሚያስችል የተጠናከረ የክትትል ስራ መስራት እንደሚኖርበት በቀድሞው ኦዲት ወቅት የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቷል፡፡

55. በክትትል ኦዲቱ ወቅት፤

- 2007 በጀት ዓመት ለአስቸኳይ ጊዜ ለልማታዊ ሴፍቲኔትና ለሌሎች ፕሮግራሞች ከአስፈጻሚ አካላት ለሚቀርብ የእህል ብድር ጥያቄ በቂ ምላሽ ለመስጠት እንዲቻል በለፉት አመታት በብድር ተስጥቶ ካልተመለሰና በ2007 በጀት አመት ከተሰጠ ብድር ውስጥ 388,388 ሜትሪክ ቶን እህል ተመላሽ እንዲሆን ለማድረግ ታቅዶ 203,856.30 ሜትሪክ ቶን 52% ብቻ ተመላሽ መደረጉ 2007 ዓ.ም ዕቅድ አፈጻጸም ላይ መገለጹ
- በ2008 ዓ.ም ዕቅድ አፈጻጸም በበጀት ዓመቱ 370,500 ሜትሪክ ቶን የምግብ እህል ከብድር ተመላሽ ገቢ በማድረግ የክምችት መጠኑን አስተማማኝ ለማድረግታ ቅዶ 208,511.5 ሜትሪክቶን 56.3% ተመላሽ የተደረገ መሆኑ፣

- በ2009 ዓ.ም ለተለያዩ ፕሮግራሞች ማስፈጸሚያ እንዲሆን ለተለያዩ ድርጅቶች ከተሰጠው ብድር 400,000 ሜትሪክ ቶን የምግብ እህል ወደ ክምችት ተመላሽ ለማድረግ ቢታቀድም 182,584.13 ሜትሪክ ቶን (45.64%) ብቻ ተመላሽ መሆኑ 2009 ዓ.ም ዕቅድ አፈጻጸም ላይ መጠቀሱ፣
- ኤጀንሲው እ.ኤ.አ ከ2014-2016 ለአደጋ መከላከል ዝግጁነትና ምግብ ዋስትና ለምግብ ዋስትና ማስተባበሪያ 129,762.93 ሜትሪክ ቶን፣ለገጠር የስራ ዕድል ፈጠራ ምግብ ዋስትና ዘርፍ ከግንቦት 2007- የካቲት 2009 ዓ.ም ድረስ 471,594.59 ሜትሪክ ቶን ፣ለኢትዮጵያ እህል ንግድ ድርጅት እ.ኤ.አ 2013 - 2017 ድረስ 395,404.59 ሜትሪክ ቶን እህል ብድር የሰጠ ቢሆንም በጠቅላላ ከሰጠው ብድር ውስጥ 571,242.7 ሜትሪክ ቶን (57.3 % ) እህል ያልተመለሰ መሆኑ ከኤጀንሱው እህል ክምችትና ስርጭት ዳይሬክቶሬት ከቀረበ የብድር ስርጭትና ተመላሽ ማስረጃ ላይ መገለጹ፣
- በአውሮፓ ህብረት በተሰጠ ዋስትና ለአደጋ መከላከልና ዝግጁነት የምግብ ዋስትና ዘርፍ እ.ኤ.አ በሜይ 02/2005 ከተወሰደው የእህል ብድር ላይ ሳይመለስ የቀረው 24,950.24 ሜትሪክ ቶን እስካሁን ድረስ ያልተመለሰ መሆኑ፣

ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል።

56. ስለጉዳዩ የኤጀንሲው ኃላፊዎች በክትትል ኦዲቱ ወቅት በቃለ መጠየቅ፣ በረቂቅ ሪፖርት እና በመውጫ ስብሰባ ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ፣ ለአደጋ መከላከልና ዝግጁነት የምግብ ዋስትና ዘርፍ እ.ኤ.አ በሜይ 02/2005 ከተወሰደው ብድር 24,950.57 ሜትሪክ ቶን ያልተመለሰ ብድር በመሆኑ የኤጀንሲውን እህል ክምችት ስለሚጎዳ ከኤጀንሲው ስቶክ ላይ እንዲቀነስ የኤጀንሲው የስራ አመራር ቦርድ በዕዳነት ከተያዘው መዝገብ እንዲሰረዝ በደብዳቤ ቁጥር አዘ10-ለ22/243 በቀን 1/03/2007 ለግብርና ሚ/ር ውሳኔው እንዲጸድቅ ያቀረበ ሲሆን የቀድሞው ግብርና ሚኒስቴር 24,950.57 ሜትሪክ ቶን እህል ጠቅላላ ዋጋ ብር 39296433.10 ከዕዳ መዝገብ ላይ ለመሰረዝ ከሚኒስቴር መ/ቤቱ የመወሰን ስልጣን በላይ በመሆኑ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ሚኒስቴር በቁጥር 01/መ16/2/11 በቀን 03/04/07 እንዲሁም በቁጥር 01/መ16/3/26 በቀን 04/08/08 እዳው እንዲሰረዝ ያቀረበ መሆኑ፣ሌሎች ለእርዳታና ለገበያ ማረጋጊያ የተሰጠው ብድር በውሉ መሰረት እንዲመለስ ያልተደረገበት ምክንያት ተበዳሪዎቹ የመንግስት አካላት በመሆናቸው ብድሩን ለመመለስ ከውጪ አገር ተገዝቶ የሚመጣው እህል ግዥውን ለመፈጸምና አንጉዞ ለማምጣት ከ4 ወር እስከ 6 ወር የሚፈጅ በመሆኑ እህሉን በውሉ መሰረት

ለመመለስ አለመቻሉን እና ግዥው በሂደት ላይ ያለ በመሆኑ እንዲመለስ ለተበዳሪዎቹ ያሳወቁ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

57. የኤጀንሲው ኃላፊዎች ይህንን ይበሉ እንጂ ለአደጋ መከላከልና ዝግጁነት የምግብ ዋስትና ዘርፍ እ.ኤ.አ በሜይ 02/2005 ከተወሰደው ብድር 24,950.57 ሜትሪክ ቶን ያልተመለሰ ሲሆን ምንም እንኳን ኤጀንሲውም ሆነ ግብርና ሚኒስቴር ብድሩ ከኤጀንሲው የብድር መዝገብ ላይ እንዲሰረዝ የተለያዩ ደብዳቤዎችን ቢጽፉም በወቅቱ ተከታትሎ ከብድር መዝገብ እንዲሰረዝ ባለመደረጉ የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

58. ኤጀንሲው ከክምችቱ ለተለያዩ ድርጅቶች በብድር የሚሰጠው እህል በወቅቱ እንዲመለስ ካላደረገ በተፈጥሮና በሰው ሰራሽ ለሚከሰት አደጋ አስቸኳይ የምግብ እርዳታ ጥያቄ ቢቀርብ ፈጣን ምላሽ ለመስጠት ሊያዳግት የሚችል ከመሆኑም በላይ የተሰጡ ብድሮች ባለመመለሳቸው ከብድር መዝገብ ላይ መሰረዝ እንደ ሀገር ለመጠባበቂያነት መያዝ ያለበትን የእህል ክምችት መጠን እንዲቀንስ ያደርጋል፡፡

## የኤጀንሲው መረጃ አያያዝ ስርዓትንበተመለከተ፤

59. በቀደመው ኦዲት ወቅትኤጀንሲው የውስጥ አሰራርን ቀልጣፋና ውጤታማ ሊያደርግ የሚችል በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ የተደራጀ ጠንካራ መረጃ አያያዝ ስርዓት የሌለው መሆኑ ታይቶ ነበር፡፡

60. የስትራቴጂክ መጠባበቂያ እህል ክምችት ኤጀንሲ የመረጃ አያያዝ ስርዓቱን በተጠናከረ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ስርዓት ሊያደራጅና ተግባራዊ ሊያደርግ እንደሚገባ የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

61. በክትትል ኦዲቱ ወቅት በናሙና ባየናቸው እና በኦዲቱ ወቅት በተካሄደ የመረጃ ክለሳና ቃለመጠይቅ ለማወቅ እንደተቻለው አስተዳደሩ የውስጥ አሠራሩን ቀልጣፋና ውጤታማ ሊያደርግ የሚያስችል በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ የተደራጀ ጠንካራ የመረጃ አያያዝ ስርዓት እንደሌለው ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

62. ስለጉዳዩ የኤጀንሲው ኃላፊዎች በክትትል ኦዲቱ ወቅት በቃለ መጠየቅ፣በረቂቅ ሪፖርት እና በመውጫ ስብሰባ ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ፣ ከቅ/ጽ/ቤቶች ጋር የመረጃን ልውውጥን በተመለከተ በኢንተርኔት፣በፋክስ ልውውጥ እንደሚያደርጉ ፣በተጨማሪም በየግዜው የእህል ክምችቱ ያለበትን ሁኔታ የመረጃ ልውውጥ እንደሚደረግ፡፡ የእህል ክምችቱን ገቢና ወጪ ለመቆጣጠር መረጃውን በኮምፒዩተራይዝድ /Automation / ለማድረግ ከፍተኛ በጀት በመንግስት በኩል ስለሚጠይቅ እና ተጠይቆም ያልተፈቀደ

በመሆኑ የተለያዩ ድርጅቶች በበጀት እንዲደግፉዋቸው ፕሮጀክት ሰርተው ያቀረቡ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

63. የኤጀንሲው ኃላፊዎች ይህንን ይበሉ እንጂ ኤጅንሲው በዳታ ቤዝ የተያዙ መረጃዎችን ማቅረብ ባለመቻሉ የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

64. ኤጀንሲው የውስጥ አሠራሩንና የመረጃ አያያዝ ስርዓቱን በተጠናከረ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ አለማደራጀቱ ተቋሙ ቀልጣፋና ውጤታማ ስራን እንዳያከናውን ያደርገዋል፡፡

## አገልግሎት የማይሰጡ ተንቀሳቃሽ የእህል ሚዛኖችን በተመለከተ፤

65. ኤጀንሲው ከህንድ አገር ካገኛቸው ከፍተኛ ተንቀሳቃሽ ሚዛኖች መካከል 7ቱ ሚዛኖች በብልሽት ምክንያት ለረዥም አመታት አገልግሎት ሳይሰጡ መቀመጣቸው በቀድሞው ኦዲት ወቅት ተገኝቶ ነበር፡፡

66. ስትራቴጂክ መጠባበቂያ እህል ክምችት ኤጀንሲ በዕርዳታ ያገኛቸውና ያለአገልግሎት የተቀመጡ የእህል ሚዛኖች ተጠግነው ስራ ላይ መዋል የሚችሉት እንዲጠገኑ ሊያደርግ ካልተቻለም እንዲወገዱ ማድረግ እንደሚጠበቅበት በቀድሞው ኦዲት የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቷል፡፡

67. በክትትል ኦዲቱ ወቅት፤

- በኤጀንሲው መጋዘን አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ስር ፡- በኮምቦልቻ ቅ/ጽ/ቤት ከሚገኙ ሚዛኖች መካከል ከአንድ(1) በስተቀር ሌሎች ሚዛን የማይሰሩ፣በመቀሌ ቅ/ጽ/ቤት ከሚገኙ 12 ትንንሽ ሚዛኖች መካከል ከአንድ(1) በስተቀር ሌሎቹ እንደማይሰሩ፣ በሽንሌ ቅ/ጽ/ቤት ከሚገኙ 11 ትንንሽ ሚዛኖች መካከል ሶስት(3) ብቻ እንደሚሰሩ፣በወላይታ ሶዶ ቅ/ጽ/ቤት ከሚገኙ 11 ሚዛኖች መካከል ሁለቱ (2) ብቻ የሚሰሩ፣በናዝሬት ቅ/ጽ/ቤት ከሚገኙ 19 ሚዛኖች መካከል አስራ ስድስቱ (16) እንደማይሰሩ ፣የወረታ መጋዘን ያሉት ተንቀሳቃሽ ሚዛንኖች የማይሰሩ መሆኑ ፣

ከተከለሱት ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

68. ስለጉዳዩ የፅ/ቤቱ ኃላፊዎች በክትትል ኦዲቱ ወቅት በቃለ መጠየቅ፣ በረቂቅ ሪፖርት እና በመውጫ ስብሰባ ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ፣ የምድር ሚዛንን በተመለከተ በዓመት ሁለት ጊዜ ኮንትራት በያዘው ድርጅት ጥገና እንደሚደረግና ከጥገና በኃላ በንግድ ሚኒስቴር ካሊብሬሽን ሥራ የሚሰራ መሆኑን፣ ተንቀሳቃሽ ሚዛኖችን በተመለከተ የተበላሹትን በመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር በኩል እንዲወገዱ አንደተደረገ ፣ የተበላሹትን በአካባቢው ባለሙያዎች እንዲጠገንና በደረጃዎች ምዘና ባለሙያዎች እውቅና እንዲሰጠው እንደሚደረግ ገልጸዋል፡፡

69. የኤጀንሲው ኃላፊዎች ይህንን ይበሉ እንጂ በክትትል በኦዲት ወቅት ያለአገልግሎት የተቀመጡ የእህል ሚዛኖች ተጠግነው ስራ ላይ ስለመዋላቸውና መጠገን የማይችሉት ተንቀሳቃሽ ሚዛኖች እንዲወገዱ የተደረገበት ማስረጃ ባለመቅረቡ የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

70. ኤጀንሲው በእርዳታ ያገኛቸውን የእህል ሚዛኖች በወቅቱ እንዲጠገኑ ወይም መወገድ ካለባቸው እንዲወገዱ ያለማድረጉ ሚዛኖቹ ያለ አገልግሎት እንዲቀመጡ እና የሚፈለገውን ውጤት እንዳያስገኙ ከማድረጉም በላይ መጋዘኖቹንም በማጣበብ አሠራር ላይ ችግር እንዲፈጥሩ ያደርጋል፡፡

## በአስተዳደሩ ስር በሚገኙ መጋዘኖች ለአደጋ ጊዜ የሚያገለግሉ የስልክ ቁጥሮች በተገቢው ቦታ መቀመጣችን በተመለከተ፣

71. በሻሸመኔ፣ በመቀሌ፣ በአዳማ፣ በወላይታ ሶዶ፣ በሽንሌና በኮምቦልቻ ስር የሚገኙ መጋዘኖች በአደጋ ጊዜ ዕርዳታ ለመጠየቅ የሚረዱ የስልክ ቁጥሮች ግልፅ በሆነና በቀላሉ ሊታይ በሚችል ቦታ ላይ ያልተቀመጡ እንዲሁም ከስራ ሰዓት ውጪ አደጋ ቢከሰት የተዘጋጀ የስልክ መደወያ ቦታ የሌለ መሆኑ በቀድሞው ኦዲት ወቅት የታየ ክፍተት ነበር፡፡

72. በመሆኑም የስትራቴጂክ መጠባበቂያ እህል ክምችት ኤጀንሲ በቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶቹ ስር በሚገኙ መጋዘኖች በአደጋ ጊዜ ዕርዳታን ለመጠየቅ የሚያስችሉ የስልክ ቁጥሮች ግልጽ በሆነ ቦታ እንዲቀመጡ ማድረግና ከስራ ሰዓት ውጪ አደጋ ቢከሰት ዕርዳታ ለመጥራት የሚያስችል የስልክ አገልግሎት ማሟላት እንደሚገባቸው የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

73. በክትትል ኦዲቱ ወቅት፤

- በአዳማ፣ በወረታና በወላይታ ሶዶ የመጋዘን አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ውስጥ በመጋዘኖች በውጨኛው በር ላይና በመጋዘኑ ውስጥ በአደጋ ጊዜ የአደጋ ጥሪ የስልክ ቁጥሮች በግልጽና በሚታይ ቦታ ተለጥፎ መገኘቱ፣
- በአዳማ፣በሻሸመኔ እና በወላይታ ሶዶ የመጋዘን አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ከስራ ሰዓት ወጪ አደጋ ቢደርስ የመስመር ስልክ ጥበቃዎች ጋር መኖሩ መሻሻል የታየበት እንደሆነ በክትትል ኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

ይሁን እንጂ በክትትል ኦዲቱ ወቅት

- በኮምቦልቻ፣ በሸንሌ፣በሻሸመኔ የመጋዘን አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ውስጥ መጋዘኖች በሚገኙበት አካባቢዎች በአደጋ ጊዜ እርዳታን ለመጠየቅ የሚያስችሉ የስልክ ቁጥሮች በግልጽና በተነበባቢ ቦታ ላይ ተለጥፈው የማይገኙ ሲሆን በመቀሌ በ 7 መጋዘኖች በአደጋ ጊዜ የአደጋ ጥሪ የስልክ ቁጥሮች ተለጥፈው የማይገኙ መሆኑን ከተከለሱ ማስረጃዎች እና በመስክ ምልከታ ለመረዳት ተችሏል፡፡

74. ስለጉዳዩ የኤጀንሲው ኃላፊዎች በክትትል ኦዲቱ ወቅት በቃለ መጠየቅ፣ በረቂቅ ሪፖርት እና በመውጫ ስብሰባ ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ፣ በቅርንጫፍ መጋዘን አስተዳደር የአደጋ ጊዜ መጥሪያ ስልኮች ቁጥሮች በመጋዘኑ በር ላይ ተጽፎ የተለጠፉ መሆናቸውና አንዳንድ ግዜ ግን በዝናብ ምክንያት ተገንጥለው ሊሆኑ እንደሚችሉ ነገር ግን አሁን ሙሉ በሙሉ በሁሉም መጋዘን ተለጥፈው የሚገኝ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

75. የኤጀንሲው ኃላፊዎች ይህንን ይበሉ እንጂ በቅርንጫፍ መጋዘን አስተዳደር የአደጋ ጊዜ መጥሪያ ስልኮች ቁጥሮች በሁሉም መጋዘኖች በር ላይ ተጽፎ እንዲለጠፍ አለመደረጉን የኦዲት ቡድኑ በመስክ የተመለከተ በመሆኑ ምክንያቱን ለመቀበል አልተቻለም፡፡

76. በቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶች በሚገኙ መጋዘኖች በአደጋ ጊዜ እርዳታን ለመጠየቅ የሚያስችሉ የስልክ ቁጥሮች ግልፅ በሆነ ቦታ አለመቀመጣቸው በመጋዘኖቹ አደጋ ቢከሰት አፋጣኝ እርዳታ እንዳይገኝ ሊያደርግ ይችላል፡፡

### በኤጀንሲው ስር በሚገኙ መጋዘኖች የእህል ህክምና ከተደረገ በኃላ ስለሚቀሩ ቁሳቁሶች አወጋገድበተመለከተ፣

77. በቀድሞው ኦዲት ወቅት በሻሸመኔ፣ በመቀሌ፣ በአዳማ፣በወላይታ ሶዶ፣ በሸንሌና በኮምቦልቻ ከእህል ህክምና በኃላ የሚቀሩ አመድና ቆርቆሮዎች በሰውና በአካባቢ ላይ ጉዳት በማያደርስ በተገቢውና ደረጃውን በጠበቀ መልኩ አለመወገዳቸው የታዩ ግኝቶች ነበሩ፡፡

78. በመሆኑም ኤጀንሲው በቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶቹ ስር በሚገኙ መጋዘኖች የእህል ህክምና ከተደረገ በኂላ የሚቀሩት አመድና ቆርቆሮዎች በተገቢው ሁኔታ እንዲቀበሩ ወይም እንዲወገዱ ማድረግ እንደሚኖርበት በቀድሞው ኦዲት የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቷል፡፡

79. በክትትል ኦዲቱ ወቅት፤

- በአዳማ ፣በወላይታ ሶዶ እና በወረታ የመጋዘን አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ውስጥ የመድሃኒት ቅሪት ማስወገጃ ደረጃውን የጠበቀ ጉድጓድ የተዘጋጀና ጉድጓዱም በቆርቆሮ

የታጠረና በቁልፍ የተዘጋጀ በር ያለው መሆኑን እና የተሻሻለ ተግባር መሆኑን በመስክ ምልከታ ለማወቅ ተችሏል፡፡

ይሁን እንጂ በክትትል ኦዲቱ ወቅት

- በኮምቦልቻ የመጋዘን አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ውስጥ የመድሃኒት ቅሪት ማስወገጃ የተዘጋጀ ቢሆንም ከእህል ህክምና በኂላ የመድሃኒት መያዥ ጣሳዎች በደንብ ተጨፍልቀው መወገድ የሚገባ ቢሆንም በደንብ ያልተጨፈለቁ ጣሳዎች ጉድጓድ ውስጥ መኖራቸውና የመድሃኒት ቅሪቱም ከቦታው ውጪ የመጋዘን ጥራት ማስወገጃ ጉድጓድ አፋፍ ላይ የሚጣል መሆኑ፣
- በሽንሌ የመጋዘን አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ውስጥ የመድሃኒት ቅሪት ማስወገጃ ጉድጓድ ደረጃውን የጠበቀ ያለመሆኑና ዙሪያውን አጥር ያልታጠረና በር የሌለው ሲሆን በተጨማሪ ከእህል ህክምና በኂላ የመድሃኒት መያዥ ጣሳዎች በደንብ ተጨፍልቀው መወገድ የሚገባ ቢሆንም በደንብ ያልተጨፈለቁ ጣሳዎች ጉድጓድ ውስጥ መኖራቸው፣
- በናሙና በታየ የሻሸመኔ መጋዘን አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ለእህል ህክምና የሚውለው የመድሃኒት ቅሪት ማስወገጃ ጉድጓድ ደረጃውን የጠበቀ ያለመሆኑና ዙሪያውን አጥር ያልታጠረና በር የሌለው ሲሆን ከመድሃኒት ቅሪት በተጨማሪ የመጋዘን ጥራጊ ቆሻሻ የሚጣልበት መሆኑ፣
- በአዳማ እና በሻሸመኔ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የሚገኙ መጋዘኖች ባለቤትነታቸው የሌላ ድርጅት በመሆኑ የእህል ህክምና ከተደረገ በኃላ ስለሚቀሩ ቁሳቁሶችና የመድሀኒት ቅሪቶች በተገቢው መንገድ እንዲወገድ አለመደረጉ፣

በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች፣ ከተደረገ ቃለ መጠይቅ እና መስክ ምልከታ ለማወቅ ተችሏል፡፡



ፎቶ ቁጥር 4፡- በሻሸመኔ መጋዘን አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ስር የሚገኘው የመድሃኒት ቅሪት ማስወገጃ ጉድጓድ ዙሪያውን አጥርና በር የሌለው

80. ስለጉዳዩ የፅ/ቤቱ ኃላፊዎች በክትትል ኦዲቱ ወቅት በቃለ መጠየቅ፣ በረቂቅ ሪፖርት እና በመውጫ ስብሰባ ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ፣ በሁሉም ቅርንጫፍ መስሪያ ቤቶች ውስጥ ደረጃውን የጠበቀ የመድሃኒት ቅሪት ማስወገጃ ጉድጓድ እንዲኖር አስፈላጊውን ጥረት ሲደረግ እንደቆየና በብዙ ቅርንጫፎች ተግባራዊ እንደሆነ ነገር ግን በዚሁ መሰረት ያልሄዱ ካሉ ወደፊት እየታየ እንደሚስተካከል ገልፀዋል፡፡

81. በኤጀንሲው ስር ባሉ መጋዘኖች የእህል ህክምና ከተደረገ በኋላ የሚቀሩት አመድና ቆርቆሮዎች በተገቢው ሁኔታ እንዲቀበሩ ወይም እንዲወገዱ አለመደረጋቸው በሰዎችና በአካባቢ ላይ ጉዳት ሊያስከትሉ ይችላሉ፡፡

### በኤጀንሲው ስር በሚገኑ መጋዘኖች ለእህል ህክምና የሚጠቀሙበትን መድሃኒት በተመለከተ፣

82. በቀድሞው ኦዲት ወቅት በሸነሌ ቅ/ፅ/ቤት ለእህል ህክምና የሚጠቀሙበት መድሃኒት ጊዜው ያለፈበት መሆኑ የታየ ግኝት ነበር፡፡

83. በመሆኑም በቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች ስር የሚገኙ መጋዘኖች ለእህል ጤንነት መጠበቂያ የሚጠቀሙባቸው መድኃኒቶች የመጠቀሚያ ጊዜያቸው ያላለፈባቸው መሆኑን ኤጀንሲው ማረጋገጥ እንደሚኖርበት የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

84. በክትትል ኦዲቱ ወቅት፤

- በሽንሌ፣ በአዳማ፣ በመቀሌና በወረታ መጋዘን አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ስር የአገልግሎት ዘመናቸው ያለፈባቸውና የማከም ብቃታቸው አነስተኛ የሆኑ 1,254.2 ኪሎ ግራም አልሙኒየም ፎስፋይድ እንዲወገዱ አለመደረጉ፣
- በአዳማ መጋዘን አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ስር የአገልግሎት ዘመኑ ያለፈበት 134.6 ሊትር ማላታይን እስካሁን ድረስ እንዲወገድ አለመደረጉ፣
- የኮምቦልቻ የመጋዘን አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ለእህል ህክምና ሲጠቀሙበት የነበረው አልሙኒየም ፎስፋይድ ስሪት ፎስ-ቶክሲን አሁን እየተጠቀሙበት ካለው አልሙኒየም ፎስፋይድ ሊትፎዝ 56% የተለየ በመሆኑ መድሃኒቱ በመጋዘኖቹ ከተጠቀሙና ህክምናው ከተደረገ አንድ ወር ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ በድጋሚ በወንፊትና በጥራጊ ላይ አንደኛና ሁለተኛ ተባዮች መታየታቸውን ገልጸው መድሃኒቱም ጥራቱን ያልጠበቀ መሆኑበን በቀን 8/2/2009 በደብዳቤ ቁጥር ከመ15/25/502 ለዋናው መስሪያ ቤት ያሳወቁ መሆኑ፣
- በወላይታ ሶዶ መጋዘን አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት አስታይል ባለ 1 ሊትር ፈሻስ አገልግሎት የማይሰጥና የመጠቀሚያ ጊዜው ያለፈበት መድሃኒት በንብረት መጋዘን ውስጥ እንዲቀመጥ መደረጉ፣

ከተከለሱ ማስረጃዎች፣ በቃለ መጠየቅ እና በመስክ ምልከታ ለማወቅ ተችሏል፡፡




ፎቶ ቁጥር 5 ፡- በወረታ፣በአዳማ እና ወላይታ ሶዶ ቅ/ጽ/ቤት ጊዜ ያለፈባቸው ፎስቶክሲን ባለ 1 ኪ/ግ፣ማላታይን እና አስታይል ባለ 1 ሊትር ፈሻስ የእህል መድሃኒት

85. ስለጉዳዩ የኤጀንሲው ኃላፊዎች በክትትል ኦዲቱ ወቅት በቃለ መጠየቅ፣ በረቂቅ ሪፖርት እና በመውጫ ስብሰባ ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ፣ ማንኛውም ዓይነት ግዜው ያለፈበት መድሃኒት በማዕከል ተሰብስቦ እንዲወገድ ለሁሉም ቅ/ጽ/ቤት መመሪያ እንዲተላለፍ መደረጉና ጊዜው ያለፈበት መድሃኒት በቅ/ጽ/ቤት ከተገኘ እንደሚከታተሉ፡፡ እንዲሁም ጊዜው ያለፈበት ማላታይን በተመለከተ መወገድ ያለበት በሀገር ደረጃ በመሆኑ እንዲወገድ ለመንግስት ንብረት አስወጋጅ መ/ቤት ያመለከቱ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

86. የኤጀንሲው ኃላፊዎች ይህንን ይበሉ እንጂ ግዜው ያለፈበት የእህል ህክምና መድሃኒት በቅ/ጽ/ቤት በሚገኝበት ወቅት ክትተል እንደሚያደርጉ የገለጹ ቢሆንም በናሙና ባየናቸው ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የአገልግሎት ዘመኑ ያለፈበትና የተበላሹ የእህል ህክምና መድሃኒቶች በቅርንጫፎች በመኖራቸው እና ለምንግስት የንብረት አስወጋጅ መ/ቤት ከማመልከት ባለፈ ክትትል አድርጎ እንዲወገድ ባለማስደረጉ ለረዥም ጊዜያት በመጋዘን ተቀምጦ የሚገኝ በመሆኑየተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

87. በቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች ስር የሚገኙ መጋዘኖች ለእህል ጤንነት መጠበቂያ የሚጠቀሙባቸው መድኃኒቶች የመጠቀሚያ ጊዜያቸው ያለፈባቸው ሆነው ለረዥም ግዜ የሚቀመጡ ከሆነ መድሃኒቱ ባለበት በአካባቢው በሚገኙ የንብረት መጋዘን ሰራተኞች ላይና በንብረት ላይ ጉዳት ሊያደርስ ይችላል ፡፡

## በኤጀንሲው ቅ/ፅ/ቤቶች ስር በሚገኙ መጋዘኖች አገልግሎት ሊሰጡ የሚችሉ ጀኔሬተሮች መኖራቸውን በተመለከተ፣

88. በቀድሞው ኦዲት ወቅት በሻሸመኔ፣ መቀሌ፣ ወላይታ ሶዶ፣ ሽንሌና ኮምቦልቻ መብራት ቢቋረት አገልግሎት ሊሰጡ የሚችሉ ጀኔሬተሮች አለመኖራቸው የኦዲቱ ግኝት ነበር፡፡

89. በመሆኑም ኤጀንሲው በስሩ በሚገኙ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች መብራት ሲቋረጥ የክምችቱ የገቢና የወጪ ስራ እንዳይስተጓጐል አገልግሎት ሊሰጡ የሚችሉ ጀኔሬተሮችን ማሟላት እንደሚጠበቅበት የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቷል፡፡

90. በክትትል ኦዲቱ ወቅት፤

- መብራት ቢቋረጥ አገልግሎች ሊሰጡ የሚችሉ ሶስት ጀኔሬተሮች በኤጀንሲው የተገዙ መሆኑና መሻሻል እንደታየባቸው ለማወቅ ተችሏል፡፡

ይሁን እንጂ በክትትል ኦዲቱ ወቅት

- በሽንሌ መጋዘን አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት በሚገኙ መጋዘኖች፣ በወረታ መጋዘን አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ከሚገኙ መጋዘኖች መካከል ከሶስት መጋዘኖች በቀር በሌሎቹ፣ በመቀሌ መጋዘን በመጋዘን ቁጥር 08 እና በኮምቦልቻ መጋዘን ቁጥር 2 የመጋዘን መብራት የሌላቸው በመሆኑ መጋዘኑ ውስጥ ያለውን የእህል ደህንነት ለመቆጣጠርና ለመፈተሽ አዳጋች ሁኔታን የሚፈጥር መሆኑ፣
- በክትትል ኦዲቱ ወቅት ናሙና በታዩ የወረታ መጋዘን አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ጀኔሬተር ባለመኖሩ መብራት በሚጠፋበት ወቅት የተቀደዱ ማዳበሪያዎችን በአዲስ ማዳበሪያ በመተካት የማዳበሪያ አፉን በማሽን ለመስፋት እና የእህሉን ደህንነት ለመቆጣጠር የሚቸገሩ መሆኑ፣

- የአዳማ መጋዘን አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት በአደጋ ስራ አመራር ግቢ ውስጥ የሚገኙ 7 መጋዘኖች ሙሉ በሙሉ መብራት የተቃጠለ እና ድጋሚ ለማሰራት ከአቅም በላይ በመሆኑና መሰራት ባለመቻሉ በስራቸው ተጽዕኖ የፈጠረባቸው መሆኑ፣
- የሻሸመኔ መጋዘን አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት የተገዛው ጄነሬተር ከተበላሸ 8 ወር የሞላው ሲሆን አገልግሎት እየሰጠ አለመሆኑ፣

ከተከለሱ ማስረጃዎች ከተደረጉ ቃለ መጠይቆች እና መስክ ምልከታ ለማወቅ ተችሏል፡፡

91. ስለጉዳዩ የፅ/ቤቱ ኃላፊዎች በክትትል ኦዲቱ ወቅት ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ፣ የመጋዘኑን ደህንነት ለመጠበቅና ተባይ እንዳይፈጠር ለመቆጣጠር መብራት ግዴታ መኖር ያለበት ሲሆን ከቅ/ጽ/ቤቶች የመብራት ችግር አለ ተብሎ እስካሁን ድረስ ሪፖርት አለመደረጉን፣ ጀነሬተርም ለሁሉም ቅ/ጽ/ቤት ገዝተው እንዳስተላለፉ፣ በሻሸመኔ ቅርንጫፉ ጄኔሬተሩ ስለመበላሸቱም መረጃው እንደሌላቸውና ችግር ካለ ወደፊት አስፈላጊውን ማስተካከያ የሚያደርጉ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

92. በቅርንጫፍ ጽ/ቤት በሚገኙ መጋዘኖች ኤሌክትሪክ አለመኖር የመጋዘኑን ደህንነት ለመጠበቅና ተባይ እንዳይፈጠር ለመቆጣጠር የሚያግዝ ሲሆን ኤሌክትሪክ ሲቋረጥ አገልግሎት ሊሰጡ የሚችሉ ጄኔሬተሮች ባለመሟላቱ የምድር ሚዛኖች ስራቸውን እንዲያቋርጡ እና እህል በቆጠራ ገቢና ወጪ እንዲደረግ ስለሚያስገድድ ይህ አሠራሩ የቁጥጥር ስርዓቱን ሊያዛባና ለብልሹ አሠራር በርሲ ከፍት ይችላል፡፡

## ክፍል ሦስት

### የመደምደሚያ ሀሳብ (Conclusion)

93. በስትራቴጂክ የመጠባበቂያ እህል ክምችት ኤጀንሲ የምግብ ክምችት አጠባበቅ በተመለከተ ኦዲት ተከናወኖ በቀረበው የኦዲት ማሻሻያ ሃሳቦች ላይ የተወሰደ እርምጃ መኖሩን ለማረጋገጥ በተከናወነው የክትትል ኦዲት የሚከተሉት መሻሻሎች እንዲሁም እርምጃ ያልተወሰደባቸው ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡፡

እነርሱም፡-

### 3.1 እርምጃ የተወሰደባቸውና መሻሻል የታየባቸው

- ንብረትነቱ የኤጀንሲው የሆነው የመቀሌና ኮምቦልቻ መጋዘን አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት የሚገኙ የምድር ሚዛኖች በ2005፣2008 እና 2009 ዓ.ም በሚመለከተው አካል የብቃት ፋተሻ /ካላብሬት/ መደረጉ፣
- የእህል ክምችትና ስርጭት ዳይሬክቶሬት እና የጥራት ቁጥጥር ስራ አመራር ዳይሮክቶሬት በቅንጅት በቅ/ጽ/ቤት በመገኘት በዕቅድና የጊዜ ሰሌዳ በማስቀመጥ የእህል ክምችት ደህንነት የጥራት ፍተሻ ስራ የሚያካሂድ መሆኑ፣
- ኤጀንሲው የእህል ኦዲትን አስመልክቶ አዲስ አሰራር በመዘርጋቱ በመጋዘን የገባው የእህል ክምችት ሙሉ በሙሉ ከመጋዘን ወጪ ሆኖ ሲያልቅ ኦዲት መደረጉ፣
- ወላይታ ሶዶ ቅርንጫፋ ጽ/ቤት በሚገኙ መጋዘኖች ለሚሰሩ የመጋዘን ክለርኮችና እና ጽዳት ሰራተኞች የእለት ተዕለት ስራዎች የሚያካሂዱበት ከመጋዘኑ ውጪ የተለየ ቢሮ መሰራቱ ፣
- በአዳማ፣ ወረታና ወላይታ ሶዶ  የመጋዘን አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ውስጥ በመጋዘኖች በውጨኛው በር ላይና በመጋዘኑ ውስጥ በአደጋ ጊዜ የአደጋ ጥሪ የስልክ ቁጥሮች  በግልጽና በሚታይ ቦታ ተለጥፎ መገኘቱ፣
- በአዳማ፣በሻሸመኔ እና በወላይታ ሶዶ የመጋዘን አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ከስራ ሰዓት ወጪ አደጋ ቢደርስ የመስመር ስልክ በጥበቃዎች ጋር መኖሩ፣
- በአዳማ ፣በመቀሌ እና በወላይታ ሶዶ የመጋዘን አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ውስጥ የመድሃኒት ቅሪት ማስወገጃ ደረጃውን የጠበቀ ጉድጓድ የተዘጋጀና ጉድጓዱም በቆርቆሮ የታጠረና በቁልፍ የተዘጋጀ በር ያለው መሆኑ፣
- መብራት ቢቋረጥ አገልግሎች ሊሰጡ የሚችሉ ሶስት ጄኔሬተሮች በኤጀንሲው የተገዙ  መሆኑ፣

## 3.2. እርምጃ ያልተወሰደባቸውና መሻሻል ያልታየባቸው

- የመቀሌ እና የኮምቦልቻ መጋዘን አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት የሚገኙ የምድር ሚዛኖች በ2006፣2007 እና 2010 ዓ.ም በሚመለከተው አካል የብቃት ፍተሻ /ካላብሬት/ ያልተደረገ መሆኑ፣
- በአዳማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ስር የሚገኘው የምድር ሚዛን የኤጀንሲው ንብረት ባለመሆኑ የምድር ሚዛኑ ካላብሬት መደረግ ከነበረበት ጊዜ ያለፈ በመሆኑ ብቃቱን በማስፈተሽ የብቃት ደረጃውን ማወቅ አለመቻሉን
- በቅርንጫፉ መጋዘን አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ስር የሚገኙት ተንቀሳቃሽ ሚዛኖች በመንግሥት ኃላፊነት በተሰጠው አካል የብቃት ማረጋገጫ እንዲያገኙ ያለመደረጉ
- በወረታ፣ በአዳማ፣ በሻሸመኔ፣ በሽንሌ እና በወላይታ ሶዶ ቅ/ጽ/ቤቶች ኤጀንሲው የራሱ የሆነ የምድር ሚዛን የሌለው በመሆኑ ፣
- በሽንሌ፣ በወላይታ ሶዶ እና በወረታ መጋዘን አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት በቅርንጫፉ የምድር ሚዛን ባለመኖሩ እህል በቆጠራ ገቢና ወጪ የሚያደርጉ መሆኑ፣
- የምድር ሚዛን ባለባቸው ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የምድር ሚዛን ቢኖርም እህል ወደ መጋዘን ገቢ እና ወጪ ሲደረግ ባለመመዘኑ በመቀሌ 27185.3 ኩንታል ፣ በሻሸመኔ 23.4 ኩንታል፣ በኮምቦልቻ 735.13 ኩንታል፣ በአዳማ 3026.83 ኩንታል በብልጫ የታየ መሆኑ
- የአዳማ መጋዘን አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት መጋዘን ቁጥር 36 እና 37 በውጪ ባለሙያ ጥገና የተደረገላቸው ቢሆንም ስራው ውጤታማ ባለመሆኑ ተመልሰው የሚያፈስ በመሆኑ አገልግሎት መስጠት የማይችሉ መሆኑ፣
- በሻሸመኔ፣ በወረታ እና በአዳማ ቅርንጫፉ ጽ/ቤቶች በሚገኙ የእህል መጋዘን በመጋዘኑ ውስጥ የጣራ ፍሳሽ በመኖሩ እህሉ እንዳይበላሽ በእስታኩ አናት ላይ ሸራ ሸፍነው እየሰሩ መሆኑ፣
- የእህል ጥራትና ተባይ ቁጥጥር ቴክኒሻኖች በመመሪያው መሰረት ወጥነት ባለው መልኩ በወር 1 ጊዜ ፍተሻ ያለመደረጉ፣
- የቅርንጫፉ ጽ/ቤት የእህል ጥራትና ተባይ ቁጥጥር ቴክኒሻኖች በመመሪያው መሰረት ወጥነት ባለው መልኩ በወር 1 ጊዜ በቅርንጫፉ ጽ/ቤት በሚገኙ የእህል መጋዘኖች ፍተሻ በማካሄድ ሪፖርት ለኤጀንሲው የማያቀርቡ መሆኑ፣
- በቅርንጫፍ ጽ/ቤት በሚገኙ  የእህል መጋዘኖች ውስጥ ሌሎች ቁሳቁሶች ፡- የተበላሹ ተንቀሳቃሽ ሚዛኖች ፣ወንበሮች፣የፅዳት ቃዎችና ቆርቆሮዎች በእህል ክምችት መጋዘን ውስጥ የተቀመጡ መሆኑ፣

- በሻሸመኔና በወላይታ ሶዶ መጋዘን የኤጀንሲው ንብረት ያልሆኑና በሰነድ ያልተመዘገቡ የሌላ መ/ቤት ንብረት የሆኑ ዱቄት፣ ጥራጥሬ እና ዘይት ከኤጀንሲው እህል ጋር በአንድ መጋዘን ተቀላቅለው የተቀመጡ መሆኑ፣
- የአዳማ፣ ወረታ፣ ሻሸመኔ፣ ወላይታ ሶዶ መጋዘን አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ለመጋዘን ኃላፊዎች፣ ጸሀፊና የጽዳት ሰራተኞች እንዲሁም በወላይታ ሶዶ ለመጋዘን ኃላፊዎች የዘውትር ስራቸውን የሚያከናውኑበት ከመጋዘኑ ውጪ የተለየ ቢሮ የሌላቸው መሆኑ፣
- በአዳማና መጋዘን አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ስር በሚገኘው የኤጀንሲው የማዕከሉ የዕቃ መጋዘን ውስጥ የተለያዩ መጠንና አይነት ያላቸው አዲስና አገልግሎት የሰጡ የእሳት ማጥፊያ ሲሊንደሮች የሚገኙ ሲሆን በየ 6 ወሩ ሰርቪስ መደረግ ቢኖርባቸውም እ.ኤ.አ በ26/5/2011 እና በ9/06/2013 ሰርቪስ እንደተደረገላቸው ተከማችተው መገኘታቸው፣
- በወረታ መጋዘን በቅ/ጽ/ቤቱ ውስጥ በሶስቱ ሸራ መጋዘን (ራቦሎች)፣ በወላይታ ሶዶ በሶስቱ ሸራ መጋዘን (ራቦሎች)፣ በኮምቦልቻ መጋዘን በመጋዘን ቁጥር 1 እና 2 ምንም የእሳት አደጋ መከላከያ መሳሪያ የሌለ መሆኑ፣
- በአዳማ፣ የወላይታ ሶዶ እና ሻሸመኔ መጋዘን አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤቶች ከ2008 ዓ.ም ወዲህ ለመጋዘን ሰራተኞቹ በእሳት አደጋ መሳሪያ አጠቃቀም ዙሪያ ስልጠና ተሰጥቶ የማያውቅ መሆኑ
- በአውሮፓ ህብረት በተሰጠ ዋስትና ለአደጋ መከላከልና ዝግጁነት የምግብ ዋስትና ዘርፍ እ.ኤ.አ በሜይ 02/2005 ከተወሰደው ብድር 24,950.57 ሜትሪክ ቶን እህል ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ከኤጀንሲው የብድር መዝገብ ላይ እንዲዘረዝ የጸደቀበት ማስረጃ ያልቀረበ በመሆኑ፣
- ኤጀንሲው እ.ኤ.አ ከ2013-2017 ለአደጋ መከላከል ዝግጁነትና ምግብ ዋስትና ለምግብ ዋስትና ማስተባበሪያ ፣ለገጠር የስራ ዕድል ፈጠራ ምግብ ዋስትና ዘርፍ እና ለኢትዮጵያ እህል ንግድ ድርጅት በጠቅላላው 996,762.11 ሜትሪክ ቶን እህል ብድር የሰጠ ቢሆንም በጠቅላላ ከሰጠው ብድር ውስጥ 571,242.7 ሜትሪክ ቶን (57.3 % ) እህል ያላስመለሰ መሆኑ፣
- የአዳማ፣ ወረታ፣ ወላይታ ሶዶ፣ ኮምቦልቻ፣ መቀሌ፣ ሽንሌ እና ሻሸመኔ መጋዘን አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤቶችን ከዋናው መ/ቤት ጋር በሰርቨር ለማገናኘት አለመቻሉ፣ ኤጀንሲው ዳታ ቤዝ ሲስተም የማይጠቀም በመሆኑ፣
- ኤጀንሲው በእርዳታ ካገኛቸው ተንቀሳቃሽ ሚዛኖች መካከል ሚዛኖች በብልሽት ምክንያት ለረዥም አመታት አገልግሎት ሳይሰጡ መቀመጣቸው እና የማይሰሩ ሚዛኖችን የሚወገዱበት ስርዓት የሌለው መሆኑ፣
- በኮምቦልቻ፣ በሽንሌ፣ በሻሸመኔ እና በመቀሌ የመጋዘን አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ውስጥ መጋዘኖች በሚገኙበት አካባቢዎች በአደጋ ጊዜ እርዳታን ለመጠየቅ የሚያስችሉ የስልክ ቁጥሮች በግልጽና በተነበባቢ ቦታ ላይ ተለጥፈው የማይገኙ መሆኑ፣

- በኮምቦልቻ፣ በሸንሌ እና በሻሸመኔ የመጋዘን አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ውስጥ የመድሃኒት ቅሪት ማስወገጃ ጉድጓድ ደረጃውን የጠበቀ ያለመሆኑ እና ከእህል ህክምና በኋላ የመድሃኒት መያዥ ጣሳዎች በደንብ ተጨፍልቀው የማይወገዱ መሆኑ፣
- በሸንሌ፣ አዳማ፣ መቀሌና ወረታ መጋዘን አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ስር የአገልግሎት ዘመናቸው ያለፈባቸውና የማከም ብቃታቸው አነስተኛ የሆኑ 1,254.2 ኪሎ ግራም አልሙኒየም ፎስፋይድ እንዲወገዱ አለመደረጉ፣
- በአዳማ መጋዘን አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ስር የአገልግሎት ዘመኑ ያለፈበት 134.6 ሊትር ማላታይን እስካሁን ድረስ እንዲወገዱ አለመደረጉ፣
- በወላይታ ሶዶ መጋዘን አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት አስታይል ባለ 1 ሊትር ፈሻስ አገልግሎት የማይሰጥና የመጠቀሚያ ጊዜው ያለፈበት መድሃኒት በንብረት መጋዘን ውስጥ እንዲቀመጥ መደረጉ፣
- በሸንሌ መጋዘን አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት በሚገኙ መጋዘኖች በወረታ መጋዘን አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ከሚገኙ መጋዘኖች መካከል ከሶስት መጋዘኖች በቀር በሌሎቹ፣ በመቀሌ መጋዘን በመጋዘን ቁጥር 08፣ በኮምቦልቻ መጋዘን ቁጥር 2 ፣ በአዳማ 7 መጋዘኖች የመጋዘን መብራት የሌላቸው በመሆኑ
  - በወረታ መጋዘን አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ጀኔሬተር የሌለ ሲሆን በሻሸመኔ መጋዘን አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት የተገዛው ጄነሬተር ከተበላሸ 8 ወር የሞላው ሲሆን አገልግሎት እየሰጠ አለመሆኑ፣

## ክፍል አራት

### የማሻሻያ ሀሳቦች (Recommendation)

94. ከላይ በክፍል ሁለት ላይ የተጠቀሱ ነባራዊ ሁኔታዎችን መሠረት በማድረግ የተደረሰባቸው መደምደሚያዎች በክፍል ሦስት ላይ ተጠቅሰዋል፡፡ በመሆኑም በመጀመሪያው ኦዲት ወቅት በተገኙ ግኝቶች ላይ የተሰጡት የማሻሻያ ሃሳቦች የተወሰኑ ነጥቦች ላይ የእርምት እርምጃ የተወሰደባቸውና ማሻሻል የታየባቸው ሁኔታዎች በመኖራቸው ተጠናክሮ መቀጠል አለባቸው፡፡

95. ነገር ግን ከዚህ በፊት በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሠረት ያልተስተካከሉና እርምጃ ባልተወሰደባቸው የኦዲት ግኝቶች ላይ ከዚህ በፊት በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት በሚመለከታቸው በሁሉም አካላት የድርጊት መርሃ ግብር ተዘጋጅቶላቸውና አስፈለጊውን ክትትል በማድረግ የእርምት እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡ የተዘጋጀውም የድርጊት መርሃ ግብርም ለመ/ቤታችን በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ መላክ አለበት፡፡

በመጨረሻም በክትትል ኦዲት ወቅት በስትራቴጂክ የመጠባበቂያ እህል ክምችት ኤጀንሲ እና በናሙና በታዩት የቅርንጫፍ መጋዘን አስተዳደር ፅ/ቤት ኃላፊዎችና ሠራተኞች ላደረጉልን የሥራ ትብብር ናመሰግናለን፡፡